## ሁለተኛው ፡ ከዲኑ ፡ የተሰጠ ፡ ዓመታዊ ፡ መግለጫ ።

## ስለ ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. የትምህርት ፡ ዓመት ፡ የተሰጠ ፡ መግለጫ ።

ከጄምስ ፡ ሲ. ኤን. ፖል ።

በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ የሕግ ፡ መምህር ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት (ፋኩልቲ) ዲን ።

### መግቢያ ።

በመጽሔቱ ፡ አዘጋጆዎች ፡ ጥያቄ ፡ የሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ የሥራ ፡ ዘመኑን ፡ ስለፈጸመው ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤታችን ፡ (ፋኩልቲ) የሥራ ፡ እርምጃ ፡ እንደ ገና ፡ የመግለጽ ፡ ዕድል ፡ በማግኘቴ ፡ ደስታ ፡ ይሰማኛል ። መግለጫዬም ፡ የሚመለከተው ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዘመን ፡ አቆጣጠር ፡ የ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. ብቻ ፡ ሲሆን ፤ ለውጭ ፡ አገር ፡ አንባቢዎች ፡ ሲባል ፡ በዚህ ፡ መግለጫ ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሱት ፡ ቀናት ፡ እንደ ፡ አውሮፓ ፡ የዘመን ፡ አቆጣጠር ፡ ናቸው ።

ኅዳር ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. በዚህ ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ (ፋኩልቲ) ተቀጣጣሪነትና ፡ አማካይነት ፡ የታቀደላቸውን ፡ የትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ ለፈጸሙት ፡ ለመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ ተማሪዎች ፡ የሕግ፡ምስክር፡ወረቀት ፡ የመስጠት ፡ የመጀመሪያው ፡ የምረቃ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ተፈጽሞአል ። በሥነ ፡ ሥርዐቱ ፡ ላይ ፡ ለተገኘነው ፡ ሁሉ ፡ ምረቃው ፡ አስደሳች ፡ ድርጊት ፡ ሆኖልን ፡ ነበር ። ሥነ ፡ በዓሉም ፡ ከፍተኛ ፡ አስተያየት ፡ የሚሰጠው ፡ መሆኑን ፡ የዩኒቨርስቲው ፡ ቻንስለር ፡ በመሆናቸው ፡ የምስክር ፡ ወረቀቱን ፡ የሰጡልን ፣ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከተናገሩዋቸው ፡ ምርጥ ፡ ቃላት ፡ መረዳት ፡ ይቻላል ።

> ግርማዊነታቸውም ፡ የሚከተለውን ፡ ተናገሩ ፤ "... አሁን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከዓለም ፡ ውስጥ ፡ ዘመናዊ ፡ የሆነ ፡ የሚያኰራ ፡ ሕግ ፡ አላት ፡ ለማለት ፡ ያስደፍራል ፤ ያስደስታልም ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ መሻሻል ፡ መጠን ፡ የሕግ ፡ ባለሞያዎች ፡ በትምህርታቸውና ፡ በሥራቸው ፡ የሰለጠኑና ፡ የተጠናቀቁ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ። የሕግ ፡ መሻሻል ፡ የአገር ፡ መሻሻል ፡ የተያያዘና ፡ የተሣመረ ፡ ነው ።
>
> በዳኝነት ፡ እውነትን ፡ መፈለግ ፡ ለሥራም ፡ ምርጥ ፡ ሰው ፡ መፈለግ ፡ ግዴታ ፡ ነው ። የሚመረጠውም ፡ ሕግን ፡ ከተማሩና ፡ ከራሣቸው ፡ ሥራቸውን ፡ ከሚያበልጡ ፡ መካከል ፡ ነው ።... ሌሎችም ፡ ይህን ፡ ምሳሌ ፡ እንዲከተሉ ፡ ተስፋ ፡ የምናደርግበት ፡ ነው ። በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ ዲግሪ ፡ የተቀበሉት ፡ ኢትዮ

ጵያውያን ፣ ጠበቆች ፡ ቁጥር ፡ እጥፍ ፡ ሊሆን ፡ መቻሉን ፡ ስናስብ ፡ መንፈሳችን የሚረካው ፡ ወደፊት ፡ የሚገጥመውን ፡ የበለጠ ፡ በብዛት ፡ እንዲገኝ ፡ ያደርገዋል፡በማለት ፡ ነው ። ዛሬም ፡ በመካከላችሁ ፡ ዳኞችና ፡ ሕግ ፡ አስከባሪዎች ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ቁጥር ፡ በመገኘታቸው ፡ ላገልግሎታቸው ፡ ትጋት ፡ ያሳየናል ።

. . . ሕግን ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ሰው ፡ ያስፈልጋል ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ የወንጀለኛ ፡ የንግድና ፡ ሌሎችም ፡ ሕጎች ፡ እንደዚሁ ፡ በፓርላማ ፡ ተመክሮ ፡ በመንግሥት ፡ የሚታወጁትን ፡ አዋጆች ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የሚያውላቸው ፡ ሰው ፡ ካላገኙ ፡ ከንቱ ፡ ጽሑፎች ፡ ሆነው ፡ ይቀራሉ ። . . . በትምህርት ፡ ራሳችሁን ፡ በማሻሻል ፡ ለባለጉዳዩ ፡ የምታቀርቡትን ፡ አገልግሎት . . . አሻሽላችኋል . . . ። ”

እነዚህም ፡ ምርጥ ፡ ቃላት ፡ በበኩሉ ፡ የሕግ ፡ ቅንጅትን ፡ ለመገንባት ፡ የሚያስችል ፡ የዕውቀት ፡ ሀብት ፡ መገኛ ፡ የሆነን ፡ ሙያን ፡ ለማደርጀት ፡ የሥራው ፡ ረዳቶች ፡ (ደጋፊዎች) ለመሆን ፡ ያለንን ፡ ዓላማ ፡ በግልጽ ፡ ያሳያሉ ። ከአርስቶትል ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እስከአለንበት ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ መልካም ፡ ገዥዎችና ፡ ፈላስፎች ፡ ሊደረስበት ፡ የሚቻል ፡ ምኞትን ፡ ለማስገኘት ፡ ለሰዎች ፡ እምነትን ፡ ለመስጠትና ፡ ነፃነታቸውንም ፡ ለመጠበቅ ፡ ተብሎ ፡ በተዘጋጀ፡ ሕግ ፡ ሥር፡ የሚተዳደሩ ፡ ካልሆኑ፡ በቀር ፤ ሰዎች፡ በነፃነትና፡ በደስታ፡ ሊኖሩ፡ ያለመቻላቸውን፡ ደጋግመው ፡ (አጉልተው) ገልጸዋል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የሕግን ፡ ተግባርና ፡ አገባብ ፡ እንደዚሁም ፡ የአፈጻጸሙን ፡ ዘዴና ፡ የተወሳሰበ ፡ መሆኑን ፡ በሚያውቁ ፡ ሰዎች ፡ የተዘጋጀና ፡ የሚካሄድ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በየትኛውም ፡ ዘመናዊ ፡ አገር ፡ ቢሆን ፡ ሕግ ፡ የተባሉትን ፡ ዓላማዎች ፡ ሊያገለግል ፡ አይችልም ። ለሕዝብ ፡ አገልግሎትና ፡ ለኢኮኖሚ ፡ ልማት ፤ ለማሕበራዊና ፡ የፖለቲካ ፡ ለውጥ ፡ ለሚያመጣ ፡ ፕሮግራም ፡ ለመፈጸም ፡ የሚያስችልና ፡ ዘወትርም ፡ ወደፊት ፡ ለሚራመድ ፡ የሕግ ፡ እድገት ፡ የተሰዋ ፡ ከፍተኛ ፡ ሙያ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በየትኛውም ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ መከበርን ፡ ሊዋጅ ፡ ( ሊማርክ ) አይችልም ።

ስለዚህ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ የሚሰጠው ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ትክክለኛ ፡ ዓላማው ፡ አገሪቱን ፡ የገጠሙዋትን ፡ ችግሮችና ፡ እነዚህንም ፡ ችግሮች ፡ ለማስወገድ ፡ የተወሰዱትን ፡ እርምጃዎችና ፡ የሕግ ፡ ሙያም ፡ በዚህ ፡ ተግባር ፡ ረገድ ፡ ያለውን ፡ አገባብ ፡ ማስጠናት ፡ ነው ። እነዚህም ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ ዓመታት ፡ በተለየ ፡ ሁኔታ ፡ በዚህ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ ውስጥ ፡ ለመሥራት ፡ ስታደልነው ፡ ሁሉ ፡ የአእምሮ ፡ አድናቆትን ፡ ሊያተርፍልን ፡ መቻሉን ፡ ከዚህ ፡ ላይ ፡ መግለጽ ፡ ያለበታው ፡ እንደተሰነዘረ ፡ እንደማይቆጠርብኝ ፡ ባለተስፋ ፡ ነኝ ።

## በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ የትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ እድገት ።

(፩) የኀሚስ ፡ ጊዜ ፡ ትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ መስፋፋት ። ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ለሦስት ፡ ዓመት ፡ የማታ ፡ ትምህርት ፡ የሚሰጥበት ፡ የሕግ ፡ ዲፕሎማ ፡ ፕሮግራም ፡ ተጀመረ ። በዚህም ፡ ፕሮግራም ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ የሚፈለገው ፡ ችሎታ ፡ ቀለል ፡ ያለ ፡ ነው ።

ይኸውም ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ፈጽሞ ፡ መገኘት ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ መምህራን ፡ በቃል ፡ ለሚጠይቁት ፡ ጥያቄ ፡ ተገቢ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ መቻልና ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ችሎታን ፡ የሚመሰክር ፡ መጠነኛ ፡ ፈተናን ፡ ማለፍና ፡ በተጨማሪም ፡ በሕግ ፤ በሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ ወይም ፡ እነዚህን ፡ መሰል ፡ በሆኑ ፡ የሥራ ፡ ስምሪቶች ፡ የሙያ ፡ ልምምድ ፡ ያለው ፡ ወይም ፡ ያላት ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ ነው ። ትምህርቱም ፡ ለመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ለጠበቆች ፡ ለሕግ ፡ አስከባሪዎች ፤ ለዳኞችና ፡ ለፓርላማ ፡ አባሎች ፡ ተብሎ ፡ የታቀደ ፡ ነው ።

በመስከረም ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ. ም. በዲፕሎማ ፡ ክፍል ፡ ዘጠና ፡ ያህል ፡ ሰዎች ፡ ተቀበልን ፤ በሰኔ ፡ ፲፱፻፷፮ ፡ ዓ. ም. አምሳ ፡ አምስት ፡ ያህል ፡ ለዓመቱ ፡ መጨረሻ ፡ ፈተና ፡ ተቀመጡ ፤ ከዚህም ፡ የበለጠ ፡ ወደፊት ፡ ቁጥራቸው ፡ እየተቀነሰ ፡ ይሄድ ፡ ይሆናል ። ሆኖም ፡ የዲፕሎማ ፡ ትምህርት ፡ ለሚጠይቀው ፡ አድካሚ ፡ ሥራ ፡ ችሎታና ፡ መንፈስ ፡ ጠንካራነት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ የሚገበዩት ፡ ትምህርት ፡ ለኑሮና ፡ ለኢትዮጵያም ፡ የሚጠቅም ፡ እንደሚሆን ፡ እናምናለን ።

ከነዚህም ፡ ተማሪዎች ፡ ጋር ፡ በመሥራታቸው ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ደስታ ፡ እንደ ተሰማቸው ፡ መምህራኑ ፡ ገልጸዋል ። ወደፊትም ፡ በዚህ ፡ ፕሮግራም ፡ የበለጠ ፡ የሥራ ፡ ትጋት ፡ እንደሚታይ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ። ከተማሪዎቹም ፡ የሚበዙት ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ከመሆናቸውም ፡ ሌላ ፡ ብዙዎቹ ፡ በቀጥታ ፡ በሕግ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የተመደቡ ፡ ናቸው ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ በመስከረም ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ. ም. ለምስክር ፡ ወረቀት ፡ ፕሮግራም ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ አዲስ ፡ ተማሪዎች ፡ ተቀብለናል ። በዚህም ፡ ፕሮግራም ፡ በሳምንት ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ከእኩለ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕጐችና ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ የመሠረታዊ ፡ ሐሳብ ፡ ትምህርት ፡ ይሰጣል ።

በዚህ ፡ ክፍልም ፡ ከሚገኙት ፡ የሚበዙት ፡ ሕግ ፡ አስከባሪዎች ፤ የመንግሥት ፡ ነገረ ፡ ፈጆች ፡ ዳኞችና ፡ ጠበቆች ፡ ናቸው ። እንደዚሁም ፡ በኅዳር ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ. ም. ከተመረቁት ፡ ቁጥራቸው ፡ ከመቶ ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ በተጨማሪም ፡ በሰኔ ፡ ፲፱፻፷፭ ፡ ዓ. ም. ሰባ ፡ ዘጠኝ ፡ ሰዎች ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ተቀብለዋል ። በአሥመራ ፡ በሚገኙ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግና ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ለማስተማር ፡ ልዩ ፡ የትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ በዚያ ፡ ጀምረናል ። እነዚህን ፡ ትምህርቶች ፡ የሚያስተምሩት ፡ ከሠራተኞቻችን ፡ አንዱ ፡ የሆኑት ፡ ሚስተር ፡ ኖርማን ፡ ሚትዝ

ገር ፡ ናቸው ። የተማሪዎቹም ፡ ብዛት ፡ ከስድሳ ፡ ሲደርስ ፤ ዳኞች ፡ ሕግ ፡ አስከባሪ
ዎችና ፡ የመንግሥት ፡ ሹማምንትም ፡ ይገኙበታል ። ረዳት ፡ ዲኑና፡እኔም ፡ ብዙ ፡
ጊዜ ፡ ወደ ፡ አሥመራ ፡ እየሄድን ፡ ጎብኝተናል ። በኛ ፡ አስተያየት ፡ እቅዱ ፡ የተ
ቃና ፡ ሆኖአል ። በጠቅላላውም ፡ ፈተናው ፡ ጥሩ ፡ ውጤት ፡ አሳይቶናል ። ተማሪ
ዎቹም ፡ በትጋት ፡ ትምህርታቸውን ፡ ይከታተላሉ ።

ኦልቁንም ፡ ተማሪዎቹ ፡ ለሌላ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግና ፡
የሕገ ፡ መንግሥት ፡ የሕዝብ ፡ መብትን ፡ ነክ ፡ ሕግ ፡ (ሪፐብሊክ ፡ ሎው ) ትምህ
ህርት ፡ ተሰጥቶአቸው ፡ በሕግ ፡ የዩኒቨርስቲውን ፡ የሕግ ፡ ምስክር ፡ ወረቀት ፡ እንዲ
ቀበሉ ፡ ይደረግላቸው ፡ ዘንድ ፡ ጠይቀዋል ።

በተጨማሪም ፡ አምሳ ፡ ያህል ፡ ሌሎች ፡ በሚመጣው ፡ ዓመት ፡ የዚሁ ፡ ዓይ
ነት ፡ ትምህርት ፡ የሚሰጥበት ፡ አዲስ ፡ ክፍል ፡ እንዲከፈትላቸው ፡ ጠይቀዋል ።
ይህንንም ፡ ጥያቄ ፡ ለሟሟላት ፡ በአሥመራ፡ ያለንን ፡ የቅጥያ ፡ ፕሮግራም ፡ ለማ
ስፋፋትና ፡ ለመቀጠል ፡ ወስነናል ። አቶ ፡ ዐማኑኤል ፡ ዐምደ ፡ ሚካኤልና ፡ አቶ ፡
ንጉሤ ፡ ፍትሕ ፡ ዐወቀ ፡ ምስጋናችን ፡ ይድረሳቸውና ፡ ባሳዩት ፡ በጐ ፡ ፈቃድ ፡
በአሁኑ ፡ የትምህርት ፡ ወቅት ፡ ተጨማሪ ፡ መምህራን ፡ ለማግኘት ፡ በመቻሉ ፡
ያሉት ፡ ተማሪዎች ፡ ትምህርታቸውን ፡ ከመቀጠላቸውም ፡ በላይ ፡ አዲስ ፡ ተማ
ሪዎችን ፡ በተጨማሪ ፡ ለመቀበል ፡ ተችሎአል ። በአሥመራ ፡ ከተማ ፡ በሚቋቋ
መው ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ አንድ ፡ አካል ፡ የሚሆን ፡ የሕግ ፡ መጻሕፍት ፡ ቤት ፡
ክፍል ፡ እንዲኖር ፡ ለማድረግ ፡ በመጠኑ ፡ የሕግ ፡ መጻሕፍት ፡ መሰብሰብ ፡ ጀም
ረናል ። የገንዘብ ፡ ዐቅማችንም ፡ ሲፈቅድልን ፡ ለመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ የሕግ ፡
ጥናት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ መጻሕፍት ፡ በሚማላት ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍቱን ፡ ወደ
ፊት ፡ ለማደርጀት ፡ እንደምንችል ፡ ባስተስፋ ፡ ነን ።

በዚሁ ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ በአማርኛ ፡ ለዲፕሎማ ፡ ደረጃ ፡ ትምህ
ርት ፡ መስጠት ፡ የሚቻልበትን ፡ ሁኔታ ፡ አጥንተናል ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በሕግ ፡ አፈ
ጻጸም ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ተመድበው ፡ ለሚገኙ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በዩኒቨርስቲ ፡ ደረጃ ፡
ከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ ለማስተማር ፡ ከተፈለገ ፡ ይህ ፡ እርምጃ ፡ በአስቸኳይ ፡ ሊወ
ሰድ ፡ የሚገባው ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

የገጠመን ፡ ችግር ፡ በአማርኛ ፡ ማስተማሪያ ፡ መጻሕፍትና ፡ ሌላም ፡ የሕግ ፡
መጻሕፍት ፡ አለማግኘት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ጥያቄው ፡ ለከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ማስተ
ማሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ በቂ ፡ ጽሑፎችን ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ለማስተርጐም ፡ እንችላለን ፡
ወይ ፡ የማለት ፡ ነው ። ልንሞክር ፡ ወስነናል ።

ዓላማውም ፡ በእርግጥ ፡ ከፍ፡ ያለ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ አሁኑኑ፡ መጀመር ፡ ይኖር
ብናል ። በዚሁም ፡ መሠረት ፡ ከመስከረም ፡ ፲፱፻፷፩፡ ዓ. ም. ጀምሮ፡ ለሦስት ፡ ዓመ
ታት ፡ ማታ ፡ ማታ ፤ በእንግሊዝ ፡ የዲፕሎማ ፡ ፕሮግራም ፡ ማስተማሪያ ፡ ጽሑፎ
ችን ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ በመተርጐምና ፡ በዚሁ ፡ ውጤት ፡ በመጠቀም ፡ በዲፕሎማ ፡

ደረጃ ፣ በአማርኛ ፣ የሕግ ፣ ትምህርት ፣ መስጠት ፣ ይጀምራል ። በእንግሊዝኛና ፣ በአማርኛ ፣ የሚሰጠውን ፣ ትምህርት ፣ በሚያስተምሩት ፣ መምህራን ፣ መካከል ፣ የቅርብ ፣ መተባበር ፣ ይደረጋል ። አንድ ፣ ዐይነት ፣ የሆነ ፣ ሥርዐተ ፣ ትምህርት ፣ በሁለቱም ፣ ቋንቋ ፣ ለማስፈጸምና ፣ አንድ ፣ ዐይነት ፣ የሆነ ፣ ፈተና ፣ ለመስጠትና ፣ የፈተናውም ፣ ውጤት ፣ አመዳደብ ፣ አንድ ፣ ዐይነት ፣ እንዲሆን ፣ ታስቦበታል ። ይኸም ፣ ሁሉ ፣ ሙከራ ፣ ነው ፤ ይሁን ፣ እንጂ ፣ ሊደከሙበት ፣ የሚገባ ፣ ሙከራ ፣ ነው ።

እነዚህ ፣ የገሚስ ፣ ጊዜ ፣ ትምህርት ፣ ፕሮግራሞች ፣ በጣም ፣ ተፈላጊ ፣ የሆነውን ፣ የሰውን ፣ ሥራ ፣ ጉልበት ፣ ለማስገኘት ፣ በማለት ፣ የታቀዱ ፣ ናቸው ። በኢትዮጵያ ፣ የሚገኙት ፣ የተማሩ ፣ ጠበቆች ፣ ቁጥር ፣ በጣም ፣ አነስተኛ ፣ ነው ፤ የተማሩ ፣ ሠራተኞች ፣ ቁጥር ፣ በማነሱ ፣ ያሉትን ፣ የሠራተኞች ፣ የሙያ ፣ ትምህርት ፣ ደረጃ ፣ ከፍ ፣ በማድረግ ፣ ለመንግሥት ፣ መሥሪያ ፣ ቤቶች ፤ ለባንኮችና ፣ ለልማት ፣ መሥሪያ ፣ ቤቶች ፣ በሕግ ፣ ሥራ ፣ የሚያገለግሉ ፣ የተማሩ ፣ ሹማምንትን ፣ ለማስገኘት ፣ መጣጣር ፣ ተገቢ ፣ መሆኑ ፣ ግልጽ ፣ ነው ።

የገሚስ ፣ ጊዜ ፣ ትምህርት ፣ ፕሮግራም ፣ ቢያንስ ፣ በሕግ ፣ የመጀመሪያ ፣ ደረጃ ፣ ትምህርት ፣ ያላቸው ፣ በርከት ፣ ያሉ ፣ ሰዎች ፣ እንደሚያስገኝና ፤ እንደዚሁም ፣ ጠለቅ ፣ ያለ ፣ ትምህርት ፣ ኖሮአቸው ፣ ከሥራ ፣ ልምምዳቸው ፣ ጋር ፣ በማጣመር ፣ የሙያ ፣ ችሎታ ፣ ያላቸውን ፣ ሰዎች ፣ ቁጥር ፣ ለማበርከት ፣ እንደሚበቃ ፣ ተስፋ ፣ አለን ።

## የዩኒቨርስቲው ፣ የኤል. ኤል. ቢ. ፕሮግራም ።

ለአገሪቱ ፣ የሕግ ፣ ዐዋቂዎችን ፣ የሥራ ፣ ጉልበት ፣ ለማበርከት ፣ በሚሰጠው ፣ በትምህርት ፣ ምኩራብ ፣ ( ፒራሚድ ) ሦስተኛ ፣ ዓመቱን ፣ የጀመረው ፣ የኤል. ኤል. ቢ. ዲግሪ ፣ ፕሮግራም ፣ እቁንጮው ፣ ላይ ፣ ሆኖ ፣ ይገኛል ። በመስከረም ፣ ፲፱፻፷፬ ፣ ለዚህ ፣ ፕሮግራም ፣ ከተቀበልናቸው ፣ ሠላሳ ፣ አዲስ ፣ ተማሪዎች ፣ አኩሌታው ፣ የመንግሥት ፣ ሠራተኞች ፣ ሲሆኑ ፤ የቀሩት ፣ ደግሞ ፣ የሁለት ፣ ዓመት ፣ የዩኒቨርስቲ ፣ ትምህርት ፣ ሲከታተሉ ፣ የቆዩ ፣ ናቸው ።

በየፈተናው ፣ ምክንያት ፣ የተማሪዎቹ ፣ ቁጥር ፣ አሁን ፣ ወደ ፣ ሀያ ፣ አምስቱ ፣ ወርዶአል ። ወደፊትም ፣ ጥቂት ፣ ሳይቀነስ ፣ አይቀርም ። ሆኖም ፣ በዚህ ፣ ክፍል ፣ መሻሻልና ፣ እንደዚሁም ፣ የሁለተኛው ፣ ዓመት ፣ የኤል. ኤል. ቢ. ተማሪዎች ፣ በሁለተኛ ፣ ዓመቱ ፣ ውስጥ ፣ የሚገኘው ፣ የማታ ፣ የኤል. ኤል. ቢ. ዲግሪ ፣ ተማሪዎች ፣ ባሳዩት ፣ ጉልሕ ፣ የሆነ ፣ መሻሻል ፣ መምህራኑ ፣ ተደስተዋል ። ለእነዚህም ፣ ተማሪዎች ፣ እስከ ፣ አሁን ፣ ባገኙት ፣ መልካም ፣ ውጤትና ፣ ለሙያ ፣ ስላላቸው ፣ አርኢያነት ፣ መልካም ፣ ምኞቴን ፣ እገልጽላቸዋለሁ ። በኤል. ኤል. ቢ. ፕሮግራም ፣ በተቻለ ፣ መጠን ፣ በጣም ፣ ሰፊና ፣ ተገቢ ፣ የሆነ ፣ ትምህርት ፣

ለመስጠት ፡ እንጣጣራለን ፡፡ የምንሠራውን ፡ በየጊዜው ፡ የመገመትና ፡ የራስንም ፡ ሥራ ፡ በነዛ ፡ ራስ፡የመቆጣጠሩ ፡ ተግባር ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ሊያቋርጥ ፡ አይገባውም ፡፡ በዚህ፡ምክንያት ፡ ፋኩልቲው፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ አራት ፡ ጥረቶችን ፡ አድርጐአል ፡፡

ሀ) ከካሊፎርኒያ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ በመጡት ፡ በፕሮፌሰር ፡ ኤም. ኤል. ሸዋርትዝ ፡ የሁለት ፡ ሳምንት ፡ ጉብኝት ፡ ምክራቸውንና ፡ ስለ ፡ ሥራችንም ፡ ያላቸውን፡ የሥራ ፡ ግምት ፡ በማግኘት ፡ ለመጠቀም ፡ ችለናል ፡፡ ፕሮፌሰር ፡ ሸዋርትዝ ፡ ብዙ ፡ የአፍሪካ ፡ ዩኒበርስቲዎችን ፡ የመጐብኘት ፡ ዕድል ፡ ያጋጠማቸው ፤ ከፍ ፡ ያለ ፡ የሥራ ፡ ልምምድ ፡ ያላቸው ፡ የሕግ ፡ መምህር ፡ ናቸው ፡፡

እርሳቸውም ፡ ስለ ፡ ሥራችን ፡ የሰጡት ፡ የሥራ ፡ ግምት ፡ መግለጫ ፡ አደፋፍሮናል ፡፡ ከኤሮፓ ፤ ከእንግሊዝና ፡ ከአሜሪካ ፡ አገር ፡ ረዘም ፡ ላለ ፡ ጊዜ ፡ የሚመጡ መምህራንና ፡ የሥራችንን ፡ ሁኔታ ፡ አመዛዝነው ፡ አስተያየታቸውን ፡ ለመስጠት ፡ የሚመጡ ፡ እንግዶች ፡ ጉብኝት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡፡ በሚመጣውም ፡ ዓመት ፡ ቢያንስ ፡ ሁለት ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጉብኝት ፡ እንደምናገኝ ፡ ባለተስፋ ፡ ነኝ ፡፡

ለ) የትምህርትን ፡ ደረጃ ፡ የሚቆጣጠር ፡ በፋኩልቲው ፡ ልዩ ፡ ኮሚቴ ፡ ተቋቁሟል ፡፡ ኮሚቴውም ፡ በተለይ ፡ አተኩሮ ፡ የተመለከተው ፤ ሐሳብን ፡ በጽሕፈት ፡ የማስፈርን ፡ ለማሻሻል ፡ ፕሮግራማችንን ፡ እንደምን ፡ አድርገን ፡ እናጠንክር ፡ ስለሚለው ፡ ጥያቄ ፡ ነው ፡፡ አዲስ ፡ (ጥሬ) የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ የበለጠ ፡ የሚማሩት ፡ በሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ ነው ፡፡ የሕግ ፡ አዋቂዎችም ፡ ሁሉ ፡ ሥራቸውን ፡ የሚያከናውኑት ፡ በጽሕፈት ፡ ነው ፡፡ ብዙ ፡ የሕግ፡ ጥበቦች ፡ በመጀመሪያ ፡ ሊገኙ ፡ የሚችሉት ፡ አዘውትሮ ፡ በመመራመርና ፡ ሥርዐት ፡ ባለው ፡ ሁኔታ ፡ የመጻፍን ፡ ችሎታ ፡ በማሻሻል ፡ ነው ፡፡ ከብዙ ፡ ስብሰባዎች ፡ በኋላ ፡ ኮሚቴው ፡ የፋኩልቲውን ፡ አባሎች ፡ ሐሳብ ፡ አጠቃሎ ፡ የሚያሳይ ፡ መግለጫ ፡ አቀረበ ፡፡

በፋኩልቲው ፡ ሥርዐተ ፡ ትምህርት ፡ መሠረት ፡ ሆኖ ፡ የሚገባውን ፡ የሦስት ፡ ዓመት ፡ እየጻፈ ፡ የመማርን ፡ ሥራ ፡ በመዘርዘር ፡ የተዋሃደ ፡ ፕሮግራም ፡ አቀረበ ፡፡ በፕሮግራሙም ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ ተማሪዎቹ ፡ ቀለል ፡ ያሉ ፕሮብሌሞችን ፡ በመተንተንና ፡ ማስታወሻ ፡ በማዘጋጀት ፡ ጀምረው ፡ ጠለቅ ፡ ወዳለ ፡ የቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ፡ ምርምር ፡ የሚያሻው ፤ ሕግ፡ የማርቀቅ ፤ በፍርድ፡ቤት፡ምስያ ፡ (ሙት ፡ ኮርት) በመካፈል ፡ እየተከራከሩ ፡ እንዲራመዱና፡ በመጨረሻው ፡ ዓመት ፡ ደግሞ ፡ ገና ፡ መፍትሔ ፡ ያላገኙ ፡ ወይም ፡ በሚስፋፉ ፡ የሕግ ፡ ክፍሎችን ፡ በሚመለከቱ ፡ አርዕስቶች ፡ ላይ ፡ በመመረቂያ ፡ ጽሑፍ ፡ ደረጃ ፡ ከፍተኛ ፡ የምርምር ፡ ጥናት ፡ እንዲያዘጋጁ ፡ ተመልክቷል ፡፡ እነዚህም ፡ ሐሳቦች ፡ በሥርዐተ ፡ ትምህርቱ ፡ ውስጥ ፡ እንዲገቡ ፡ ተደርጐአል ፡፡ በዚህ ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ለምሳሌ ፡ ያሀል ፡ የአስተዳደር ፡ ሕግና ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ የሚያጠኑት ፡ ተማሪዎች ፡ "በኢትዮጵያ፡ በዋስትና ፡ ወረቀት ፡ የመለቀቅ" እና ፡ "የብሔራዊ ፡ ቡና ፡ ቦርድ ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም" በሚሉ፡ አርእስቶች ፡ የአንድ ፡ ትምህርት ፡ ወራት ፡ ጊዜ ፡

ጽሑፍ ፡ ጽፈው ፡ አቅርበዋል ። ብዙ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ መመራመርንና ፡
በየሥፍራው ፡ እየተዘዋወሩ ፡ መጠያየቅን ፡ የሚያስከትሉ ፡ ጽሑፎች ፡ በተማሪ ፡
ዎቹ ፡ ተጽፈዋል ።

ከነዚሁም ፡ የተሻሉት ፡ የኢትዮጵያን ፡ የሕግ ፡ ዕውቀት ፡ በጣም ፡ እንደሚያ
በለጸጉት ፡ እየተማመንን ፡ ከነዚሁም ፡ ጥቂቶቹን ፡ ፋኩልቲው ፡ አሳትሞ ፡ የሚያ
ወጣበትን ፡ ቀን ፡ በናፍቆት ፡ እጠባበቃለሁ ።

ሐ) የፋኩልቲው ፡ የትምህርትን ፡ ደረጃ ፡ የሚቆጣጠር ፡ ኮሚቴ ፡ ዓመቱን ፡
በሙሉ ፡ ጠቅላላውን ፡ ፕሮግራም ፡ አጥንቶአል ። ምንም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ በሕግ ፡
መምህራን ፡ መካከል ፡ ስለ ፡ ሥርዐተ ፡ ትምህርቱ ፡ ዝርዝር ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ መስ
ማማት ፡ አይኖር ፡ ይሆናል ፤ በኔ ፡ አስተያየት ፡ ሥርዐተ ፡ ትምህርት ፡ የማይለወጥ ፡
ሁኖ ፡ መታየት ፡ የለበትም ። ሆኖም ፡ አንዳንድ ፡ መሠረታዊ ፡ ውሳኔዎች ፡ ተወስ
ነዋል ። ፋኩልቲው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተገለጸው ፡ በመመረቂያ ፡ ጽሑፍ ፡ ደረጃ ፡
ከፍተኛ ፡ የምርምር ፡ ጥናት ፡ ማዘጋጃ ፡ ፕሮግራምና ፡ ለዚህም ፡ በቂ ፡ ጊዜ ፡ እንዲ
ሰጠው ፡ ይሁን ፡ ለተባለው ፡ ሐሳብ ፡ ተስማምቶአል ።

እንደዚሁም ፡ ከመጀመሪያዎቹ ፡ ተመራቂዎቻችን ፡ የሚበዙት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡
ሚኒስቴሮች ፡ አማካይነት ፡ በአስተዳደር ፡ ሥራ ፡ እንደሚቀጠሩና ፡ የከፍተኛ ፡ ሕጎ
ችን ፡ ረቂቅ ፡ ወይም ፡ የአፈጻጸም ፡ ደንቦችን ፡ እንዲያዘጋጁ ፡ እንደሚጠየቁ ፡ በመ
ገመት ፤ በሕግና ፡ በልማት ፡ መሪ ፡ ሐሳቦች ፡ ( ፖሊሲ ) አወሳሰን ፡ መካከል ፡ ስለ
ሚኖረው ፡ ግንኙነት ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ አስተያየት ፡ እንዲኖራቸው ፡ በማሰብ ፡ ከሥር
ዐተ ፡ ትምህርታችን ፡ መካከል ፡ የሕዝብ ፡ መብትን ፡ ነክ ፡ ሕግ ፡ ( ፐብሊክሎው )
ከፍ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ ተሰጥቶታል ። ምክንያቱም ፤ ሕግን ፡ ማዘጋጀትና ፡ ሕግን ፡ ማስ
ፈጸም ፡ የልማት ፡ ፕሮግራሞች ፡ የሚፈጸሙባቸው ፡ መሣሪያዎች ፡ በመሆናቸው ፡
ነው ። ተራ ፡ ሰዎች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ሕግን ፡ ማርቀቅና ፡ ማስፈጸም ፡ የመንግሥ
ትን ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ሐሳቦች ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ በማዋል ፡ ረገድ ፡ የሚወስድ ፡ የቅል
ጥፍና ፡ ስምምሙ ፡ የሆነ ፡ ዘዴ ፡ አድርገው ፡ ይገምቱታል ። እርግጡ ፡ ነገር ፡ ግን ፡
እንዲህ ፡ አይደለም ።

ሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ ከፍተኛ ፡ ስለሆነው ፡ አዳዲስ ፡ ብሔራዊ ፡ ሕጎች ፡ ዓላማና
ችግር ፡ በሰፊው ፡ እንዲያውቁ ፡ ካልተደረገ ፡ እና ፡ የሕግ ፡ አዘጋጂነት ፤ አማካሪ
ነት ፡ ወይም ፡ አስፈጻሚነት ፡ ተግባርን ፡ ሥርዐት ፡ ባለውና ፡ በተሟላ ፡ ሁኔታ ፡
ሊፈጸሙ ፡ እንዲችሉ ፡ ካልተደረገ ፤ ሞያቸውም ፡ በሚገባው ፡ መንገድ ፡ ካልተመ
ራ ፡ በቀር ፤ የሚታቀደው ፡ ታላቅና ፡ ጠቃሚ ፡ መሻሻል ፡ ወይም ፡ ለውጥ ፡ ሁሉ ፡
በወረቀት ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ የሰፈረ ፡ በገቢር ፡ የማይገለጽ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። በማደግ ፡
ላይ ፡ በሚገኙ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ የከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ የሰው ፡ የሥራ ፡ ጉልበት ፡ ፍላ
ጎት ፡ ፅንሰ - ሐሳብ ፡ ጉዳይ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተገቢው ፡ ግምት ፡ የሚሰጠው ፡ አይመ
ስለኝም ። በአገር ፡ እድገት ፡ ጉዳይ ፡ “ እንደመሐንዲሶች ” ሕግ ፡ ዐዋቂዎችም ፡

ርሻ ፡ ተግባራቸውን ፡ በሚገባ ፡ እንዲፈጽሙ ፡ ያስፈልጋል ። ስለዚህ ፡ ማስተማር ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሕገ ፡ መንግሥትን ፡ የሕግ ፡ አወጣጥና ፡ የአስተዳደር ፡ ሥነ ሥርዐትን ፡ ጠቅላላ ፡ ሁኔታ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ በሕግ ፡ በአስተዳደር ፡ አመራርና ፡ በኢኮኖሚ ፡ ልማት ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ በተመሰጠ ፡ አኳኋን ፡ የሚያስረዱ ፡ የተመረጡ ፡ ሁኔታዎችን ፡ ጠለቅ ፡ ብሎ ፡ ማጥናትም ፡ ያሻል ።

በዚህም ፡ መሠረት ፡ “ ሕግና ፡ የመንግሥት ፡ የኢኮኖሚ ፡ ሥራ ፡ መሪ - ሐሳብ ” ተብሎ ፡ የተሰየመ ፡ ዓመቱን ፡ በሙሉ ፡ የሚሰጥ ፡ የከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ለማስተማር ፡ አስበናል ። ይኸውም ፡ ትምህርት ፡ በተቀዳሚ ፡ የልማት ፡ እቅድ ፡ የእቅዱ ፡ ዝግጅትና ፡ ሕጋዊ ፡ አግባቡን ፡ ይመለከታል ። በተጨማሪም ፡ የቀረጥ አወሳሰንና ፡ አሰባሰብን ፡ ችግሮች ፡ ማለት ፡ ገቢ ፡ የማግኛ ፡ ዘዴዎች ፡ የሚ ፡ ደረጃበትን ፤ የቀረጥ ፡ ሕጎችን ፡ የማዘጋጀትና ፡ ፍች ፡ መስጠትን ፤ እንደዚሁም ፡ የቀረጥን ፡ አስተዳደር ፡ የሚነኩ ፡ ችግሮችን ፡ ይመረምራል ። እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፤ ገንዘብን ፡ (ሀብትን ) አጥቅም ፡ ላይ ፡ ስለማዋል ፡ በወጡ ፡ የመንግሥት ፡ የንግድ ማኅበሮችን ፡ የሚያቋቁሙ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የባንክ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ ሕጎችና ፡ እንዲሁም ፡ እነዚህን ፡ በመሳሰሉ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጎች ፡ ውስጥ ፡ እንደተመለከተው ፡ ሁሉ ፡ የንግድን ፡ ልማት ፡ ለማሻሻል ፡ የሚረዱ ፡ የመንግሥት ፡ የሥራ ፡ መሪ ፡ ሐሳብና ፡ እርምጃ ፡ ምን ፡ እንደሆኑ ፡ ያጠናል ። በዚህም ፡ ረገድ ፡ ብዙና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥናትና ፡ ምርምር ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ። እነዚህም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አስፈላጊና ፡ ለአእምሮም ፡ አንቂነት ፡ የተለዩ ፡ ጐዳና ፡ ይሆናሉ ፡ ብለን ፡ ተስፋ ፡ ካደረግናቸው ፡ ውስጥ ፡ ለምሳሌ ፡ ብቻ ፡ የተጠቀሱ ፡ ናቸው ።

መ) ከሕግ ፡ ትምህርት ፡ በፊት ፡ የሚሰጥ ፤ ከዩኒቨርስቲው ፡ የፋኩልቲ ፡ ጉባኤ ፡ በተሰጠን ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ በአርትስ ፡ ፋኩልቲ ፡ ውስጥ ፡ ከሕግ ፡ ትምህርት ፡ በፊት ፡ የሚሰጥ ፡ ትምህርት ፡ ማስተማር ፡ ጀምረናል ። በዚሁም ፡ መሠረት ፡ ቁጥራቸው ፡ የተወሰነ ፡ የዩኒቨርስቲ ፡ ተማሪዎች ፡ በመጀመሪያ ፡ ዓመት ፡ የዩኒቨርስቲ ፡ ትምህርታቸው ፡ መጨረሻ ፡ ይኸን ፡ ትምህርት ፡ የመምረጥ ፡ ዕድል ፡ ይኖራቸዋል ።

ሥርዓተ ፡ ትምህርቱ ፡ ከአርት ፡ ፋኩልቲ ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ የሚዘጋጁ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ እነዚህ ፡ ተማሪዎች ፡ ለሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ የዩኒቨርስቲ ፡ ትምህርታቸው ፡ በአርት ፡ ፋኩልቲ ፡ ከሚሰጡት ፡ የትምህርት ፡ ዐይነቶች ፡ መካከል ፡ ምርጫ ፡ ይፈቀድላቸዋል ። በተጨማሪም ፡ ኢትዮጵያን ፡ በሚመለከቱ ፡ የተመረጡ ፡ ችግሮችን ፡ በመመርመር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሕግን ፡ መማሪያ ፡ ዘዴዎችን ፡ እንዲያውቁ ፡ የመለማመጃ ፡ ትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ ይኖራቸዋል ። በዓመቱም ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ የፈተናቸው ፡ ማዕከላዊ ፡ ውጤት ፡ የሚያስደስት ፡ ሁኖ ፡ ከተገኘ ፤ ወደ ፡ ሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ተዛውረው ፡ ለሦስት ፡ ዓመት ፡ የሕግ ፡ የሞያ ፡ ጥናት ፡ እንዲከታተሉ ፡ ይደረጋል ።

" ከሕግ ፡ ትምህርት ፡ በፊት ፡ የሚሰጥን ፡ ትምህርት" ፕሮግራም ፡ በመደገፍም ፡ ሆነ ፡ በመቃወም ፡ ብዙ ፡ መናገር ፡ ይቻላል ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ያለንበት ፡ ሁኔታ ፡ በጥብቅ ፡ እናስብበት ፡ ዘንድ ፡ የሚያስገድድ ፡ ነው ። ከሁሉ ፡ በፊት ፡ በጊዜው ፡ ሁኔታ ፤ በተለይም ፤ ከፍተኛ ፡ ወጭ ፡ በሚያስፈልገው ፡ የዩኒቨርስቲ ፡ ትምህርት ፡ ምክንያት ፤ ለሕግ ፡ የሞያ ፡ ትምህርት ፡ የመግቢያ ፡ ደረጃ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ የዩኒቨርስቲ ፡ ትምህርት ፡ መጨረሻ ፡ እንዲሆን ፡ ለማድረግ ፡ ተገድደናል። ይኸም ፡ ማለት ፤ ከፍተኛና ፡ ሰፊ ፡ ለሆነው ፡ የሞያ ፡ ትምህርት ፡ ተማሪዎችን ፡ በጣም ፡ አጭር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ማዘጋጀት ፡ አለብን ፡ ማለት ፡ ነው ። የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ነክ ፡ የሳይንስ ፡ ትምህርቶች ፡ ለማሳወቅና ፡ የመገናኛ ፡ ዘዴዎች ፡ ( በቋንቋ ፡ ችሎታ ) በማሻሻል ፡ ረገድ ፡ ሰፊ ፡ የሆነ ፡ ትምህርት ፡ መስጠት ፡ ያሻል ።

የወደፊት ፡ የሕግ ፡ ዐዋቂዎች ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ ስለሚገጥማቸው ፤ ሰፊና ፡ ጠንካራ ፡ የሆነ ፡ ጠቅላላ ፡ የትምህርት ፡ መሠረት ፡ እንዲኖራቸው ፡ የሚያስፈልግ ፡ መሆኑን ፡ ስለማምን ፤ በኔ ፡ አስተያየት ፤ በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ መግቢያ ፡ ደረጃን ፡ ወደፊት ፡ ከፍ ፡ ለማድረግ ፡ ማሰብ ፡ ይኖርብናል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እንደ ዚህ ፡ ያለው ፡ ጉዳይ ፡ ወደፊት ፡ የበለጠ ፡ ጥናት ፡ በማድረግ ፡ የሚወሰን ፡ ነው ፤ ለጊዜው ፡ ግን ፡ ተገቢው ፡ ችሎታ ፡ ያላቸውን ፡ ተማሪዎች ፡ ለሕግ ፡ ትምህርት ፡ ለመምረጥ ፡ በመቻላችንና ፡ እንደዚሁም ፡ ለሚከተሉት ፡ ሁለት ፡ ዓመታት ፡ ቢያንስ ፡ ሀያ ፡ ተማሪዎች ፡ ከዩኒቨርስቲው ፡ በየዓመቱ ፡ ለማግኘት ፡ እንደምንችል በማወቃችን ፡ ተደስተናል ።

<u>ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጻሕፍት ፡ ዝግጅትና ፡ መታተም</u> ።

የማስተማሪያ ፡ መጻሕፍት ፤ የሕግ ፡ አስተያየት ፡ መግለጫ ፡ አለመኖርና ፤ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የተሰጡት ፡ ውሳኔዎች ፡ ታትሞ ፡ አለመውጣት ፡ በቀላሉ ፡ የሚገመት ፡ ችግር ፡ አይደለም ። እንደነዚህ ፡ ያሉት ፡ ጽሑፎች ፡ በብዛት ፡ የሌሉት ፡ ማናቸውም ፡ የሕግ ፡ ሙያተኛ — አሳቢ ፡ የሕግ ፡ ዐዋቂ — እምሀበ ፡ አልቦ ፡ እንደሚሠራ ፡ የሚቆጠር ፡ ነው ። እነዚሀ ፡ መሣሪያዎች ፡ ለማንኛውም ፡ ዘመናዊና ፡ የተስተካከለ ፡ የሕግ ፡ አመራር ፡ በእርግጥ ፡ የደም ፡ ሥሮች ፡ ናቸው ።

በትጋት ፡ በሚሠራው ፡ በፋኩልቲው ፡ ኮሚቴ ፡ አማካይነት ፡ የታቀደው ፡ ፕሮግራማችን ፡ <u>የኢትዮጵያን ፡ ፍላጎቶች</u> ፡ የሚያሟሉ ፡ <u>የኢትዮጵያን</u> ፡ የሕግ ፡ መጻሕፍት ፡ አዘጋጅቶ ፡ የማውጣት ፡ ዓላማ ፡ ያለው ፡ ነው ። በዚሁም ፡ መሠረት ፡ ፋኩልቲው ፡ ከተቋቋመበት ፡ የሁለት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የሚከተሉትን ፡ የመጀመሪያ ፡ ተግባሮች ፡ ፈጽሞአል ።

(፩) <u>የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት</u> ። ከፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ በአማርኛና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ይህን ፡ መጽሔት ፡ ማሳተም ፡ ጀምረናል ። በዚሁም ፡

አማካይነት ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔዎችንና ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ አስተያየት ፡ መግለጫዎች ፡ መታተም ፡ ጀምረዋል ። መጽሔቱም ፡ በየመንፈቁ ፡ ታትሞ ፡ የሚወጣ ፡ ሲሆን ፡ የአዘጋጅ ፡ ኮሚቴ ፡ አባሎች ፡ ሽያጩን ፡ ለማብዛት ፡ ባደረጉት ፡ ብርቱ ፡ ጥረትና ፡ የሕዝብ ፡ ማስታወቂያ ፡ በውስጡ ፡ በማሳተም ፡ ይልቁንም ፡ የመጽሔቱ ፡ ደጋፊዎች ፡ በመሆን ፡ የሚረዱ ፡ ሰዎች ፡ ለማግኘት ፡ በአደረግነው ፡ ሙከራ ፡ አጥጋቢ ፡ ውጤት ፡ በማግኘቱ ፡መጽሔቱ ፡ ወጭውን ፡ እራሱ ፡ የሚችል ፡ ለመሆን ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አልቀረው ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የመጽሔቱ ፡ ጠባቂዎችና ፡ ደጋፊዎች ፡ በመሆን ፡ ሀያ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ የከፈሉት ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ በመጽሔቱ ፡ መጀመሪያ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ በዝርዝር ፡ ተመልክቶ ፡ ይገኛል ። የነዚህም ፡ ሰዎች፡ ዕርዳታ፡ መጽሔቱን፡ ለማሳተም፡ እንዲቻል፡ በማለት፡ ለጠበቆች፡ ወይም ፡ ለሕግ ፡ አዋቂዎችና ፡ ለዳኞች ፡ ለቀረበው ፡ ሕዝባዊ ፡ ልመና፡አስደሳች ፡ መልስ ፡ ነው ። የሥራ ፡ ጓደኞቼ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሬደን ፤ ሚስተር ፡ ሉውንሽቴን ፡ ሚስተር ፡ ኪንድረድ ፤ ሚስተር ፡ ሲንገርና ፡ሚስተር ፡ ፊሸር፡ በመጽሔቱ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ሰዓቶች ፡ የሚያሳልፉ ፡ መሆኑን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ሳልገልጸው ፡ ላልፍ ፡ አልፈቅድም ። እንደዚሁም ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ከተማሪዎቹ ፡ መካከል ፡ አራት ፡ አባሎች ፡ በአዘጋጁ ፡ ኮሚቴ ፡ ውስጥ ፡ መግባታቸውና ፡ ስማቸውም ፡ በመጽሔቱ ፡ መግቢያ ፡ ላይ ፡ የሚመለከት ፡ መሆኑን ፡ ልገልጽ ፡ እወዳለሁ ። የሠሩትም ፡ ሥራ ፡ የሚመሰገን ፡ ነው ። ይኸ ፡ የመጀመሪያው ፡ ሲሆን ፡ መጽሔቱን ፡ በማዘጋጀት ፡ ሥራ ፡ ተማሪዎችም ፡ ተካፋይ ፡ የመሆናቸው ፡ ልማድ ፡ ለወደፊትም ፡ የሚቀጥል ፡ ሆኖ ፡ የመጽሔቱን ፡ ሳያቋርጥ ፡ መውጣት ፡ የሚያረጋግጥ ፡ እንደሚሆን ፡ ባለተስፋ ፡ ነን ።

(፪) የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ያሳተማቸው፡ መጻሕፍት ። በሐምሌ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፷፩፡ ዓ. ም. የመጀመሪያዎቹን ፡ ሦስት፡ መጻሕፍትን፡ አሳትመናል። እነዚሁም፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፤ የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መግቢያ ፡ ( ከቁ. ፩ ፡ እስከ ፡ ፻፬ ) በሚል ፡ አርእስት ፡ በዶክተር ፡ ፊሊፕ ፡ ግራቬን ፡ የተዘጋጀው ፡ መጽሐፍ ፤ የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የጠቅላላው ፡ ክፍል ፡ የመጀመሪያው ፡ አስተያየት ፡ መግለጫ ፤ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ኮሚሲዮንን ፡ ማስታወሻና ፡ በሕግ ፡ በኩል ፡ የስዊስንም ፡ ነቅዕ - መነሻ ፡ የሚጠቅስ ፡ ነው ።

ሁለተኛ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በስዊዘርላንድ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ አንፃፃሪ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ጽሑፎች ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ በስቲቨን ፡ ለውንሽቴን ፡ የተዘጋጀው ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ። በዚሁም ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ከኢትዮጵያ ፤ ከስዊስና ፡ ከሌሎችም ፡ ነቅዕ - መነሻዎች ፡ የተገኙ ፡ ጽሑፎችና ፡ ከሕግ ፡ ቃሎች ፡ ሌሎችም ፡ ማስታወሻዎች ፡ የኢትዮጵያን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ለማስተማሪያ ፡ እንዲያገለግሉ ፡ የተዘጋጁ ፡ ጥያቄዎችና ፡ ምርምሮች ፡ ተጠቃለው ፡ ይገኙበታል ።

ሦስተኛው ፡ ደግሞ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሕጎች ፡ መጋጨት ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ በሮበርት ፡ አለን ፡ ሲድለር ፡ የተዘጋጀው ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ መጽሐፍ ፡ የሕጎች ፡ መጋጨትን ፡ ታሪካዊ ፡ ሁኔታና ፡ በጠባያቸውም ፡ የሚነገሩትን ፡ እምነቶች ፡ የሚያትትና ፡ በኢትዮጵያም ፡ በዚሁ ፡ ረገድ ፡ ወደፊት ፡ የሚደርሰውን ፡ እድገት ፡ የሚገልጽ ፡ ነው ።

በተጨማሪም ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሬደን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕጋዊ ፡ ሞዴል ፡ (ፎርም) መጽሐፍ ፡ በማዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ናቸው ። በዚሁም ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕጋዊ ፡ ሞዴሎች ፡ ከነመቅድማቸው ፡ እንደዚሁም ፡ የንግድ ፡ ሞዴል ፡ የኪራይ ፡ ስምምነቶች ፡ የውል ፡ (የኮንትራት) ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ዶኪማዎችና ፡ እነሱን ፡ የመሳሰሉትም ፡ ለዓይነት ፡ ያህል ፡ ይገኙበታል ። ይኸውም ፡ ለማስተማሪያ ፡ የሚጠቅም ፡ መጽሐፍ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ለሕግ ፡ ሙያም ፡ የሚበጅ ፡ እንደሚሆን ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

(፫) ስለ ፡ መሬት ፡ ይዞታ ፡ የተዘጋጁ ፡ መጻሕፍት ፡ መታተም ፤ የመሬት ፡ ሕግና ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ ለማሻሻል ፤ እንደዚሁም ፡ የንብረት ፡ ሕግ ፡ በሚገባ ፡ ለማስተማር ፡ አስቀድሞ ፡ አሁን ፡ ያለው ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ ሥሪት ፡ በይበልጥ ፡ ሊታወቅ ፡ ይገባል ። የኢትዮጵያ ፡ ምርምርና ፡ ጥናት ፡ ኢንስቲትዩት ፡ ከሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ የሚገልጽ ፡ ጽሑፎችን ፡ ለማሳተም ፡ ወስኗል ። የመጀመሪያዎቹም ፡ ሁለቱ ፡ መጻሕፍት ፡ ታትመዋል ። እነዚህም ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

የመጀመሪያው ፡ የሰሜን ፡ ኢትዮጵያ ፡ መሬት ፡ ሥሪት (ቻርተርስ) በሚል ፡ አርእስት ፡ በለንደን ፡ ዩኒበርስቲ ፡ የምሥራቃዊና ፡ የአፍሪካ ፡ ጥናት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ፕሮፌሰር ፡ በሆኑት ፡ በዶክተር ፡ ጂ. ደብሊው. ቢ. ሀንቲንግ ፡ ፎርድ ፡ የተዘጋጀው ፡ ነው ። ይኸውም ፡ በቆየው ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ ነገሥታቱ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ለመኳንንት ፡ መሬት ፡ የሰጡባቸው ፡ ማስረጃዎች ፡ ምርምር ፡ ነው ።

ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ በሸዋ ፡ ውስጥ ፡ በሚገኘው ፡ በቆሬ ፡ የተደረገ ፡ የመከራ ፡ ጥናት ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ የምግብና ፡ የእርሻ ፡ ድርጅት ፡ የገጠር ፡ አጥኚዎች ፡ ሹም ፡ በሆኑት ፡ በዶክተር ፡ ኤች. ኤስ. ማን ፡ የተዘጋጀው ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ጽሑፍ ፡ በደቡባዊ ፡ ሸዋ ፡ ለዐይነት ፡ በተመረጠ ፡ በአንድ ፡ አነስተኛ ፡ ሥፍራ ፡ የተደረገውን ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ ጥናት ፡ የሚያስረዳ ፡ ሲሆን ፤ የይዞታውን ፡ መበላለጥና ፡ ከመሬት ፡ ይዞታ ፡ ጋር ፡ የተያያዘውን ፡ የኢኮኖሚና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ሁኔታም ፡ ይገልጻል ። በተለይም ፡ በዚሁ ፡ ሥፍራ ፡ በባለመሬትና ፡ በጭሰኛ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ አስፋፍቶ ፡ ያስረዳል ።

(፬) የማስተማሪያ ፡ መማሪያዎች ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ምንጮች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ በጣም ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው ።

ሀ) የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ዋና ፡ ምንጩ ፡ የስዊስ ፡ ሕግ ፡ ( ኮድ ) ሲሆን ፡ ከዩጎዝላቪያ ፡ ከግሪክና ፡ ከብራዚል ፤

ለ) የፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ደግሞ ፡ ከፈረንሣይና ፡ ከጀርመን ፤

ሐ) የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፤ በሕንድ ፡ አማካይነት ፡ ከኮመን ፡ ሎው ፡ የተገኙ ፡ ሐሳቦች ፡ የሚገኙባቸው ፡ ሲሆን ፤ እንደዚሁም ፤

መ) ሕገ ፡ መንግሥቱና ፡ ብዙ ፡ የአስተዳደር ፡ ሕጎች ፡ ደግሞ ፡ መሠረታቸው ፡ በከፊል ፡ ከእንግሊዙ ፡ አሜሪካን ፡ ምንጭ ፡ ሁኖ ፡ ይገኛል ።

የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ በውጭ ፡ የሕግ ፡ መጻሕፍትና ፡ ጥናቶች ፡ ለማስተማር ፡ አይቻልም ። የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ ለማስተማር ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ሥርዐትና ፡ የአገሪቱን ፡ አቋሞችና ፡ ተለዋዋጭ ፡ ፍላጎቶች ፡ በተለይ ፡ የሚመለከቱ ፡ መጻሕ ፍት ፡ ያስፈልጋሉ ። ስለዚህ ፡ ለእያንዳንዱ ፡ የትምህርት ፡ ዐይነት ፡ የተለየ ፡ የማ ፡ ስተማሪያ ፡ ጽሑፍ ፡ ማሰናዳት ፡ የያንዳንዱ ፡ የፋኩልቲው ፡ አባል ፡ ( መምህር ) ፡ ዐይነተኛ ፡ ተግባር ፡ ነው ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ የማስተማሪያ ፡ ጽሑፎች ፡ ተዘጋጅተው ፡ በማባዣ ፡ መኪና ፡ እየተባዙ ፡ ይሠራባቸዋል ። እነዚህም ፡ ጽሑፎች ፡ የሚያገለግሉት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ጽሑፎችን ፤ ሕጎችና ፡ ጉዳዮችን ፡ ከዛሬይቱ ፡ ኢት ዮጵያ ፡ ጋር ፡ ለማዛመድ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሊገኙ ፡ የቻሉትን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጽሑ ፎችም ፡ በማስተባበር ፡ ተማሪዎች ፡ ጠቃሚውን ፡ የሕግ ፡ ጥበብ ፡ እንዲገበዩና ፡ የገዛ ፡ ራሳቸው ፡ የሆነ ፡ ነፃ ፡ አስተሳሰብ ፡ እንዲኖራቸው ፡ ለማበረታታት ፡ የታ ቀዱ ፡ ጥያቄዎችና ፡ መግለጫዎችን ፡ ለማቅረብ ፡ ጭምር ፡ ነው ። በነዚህም ፡ መጻሕፍት ፡ ተማሪዎቹ ፡ እንደመማሪያ፡ ይጠቀሙባቸዋል ። እነዚህም ፡ የተባዙ ፡ የማስተማሪያ ፡ መጻሕፍት ፡ እንደተጣሩና ፡ እንደተሟሉ ፡ ወዲያውኑ፡ ይበልጥ ፡ ነዋሪ ፡ በሆነ ፡ እኳኋን ፡ ታትመው ፡ እንዲገኙና ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ባለሞያ ዎችና ፡ የተማሪዎችም ፡ መጠቀሚያ ፡ ለመሆን ፡ እንደሚበቁ ፡ የፋኩልቲው ፡ ተስፋ ፡ ነው ። ይኸም ፡ ሲሆን ፡ የፋኩልቲውን ፡ የወደፊት ፡ አባሎች ፡ ጊዜያቸውን ፡ ሌላ ፡ ከፍተኛ ፡ የምርምር ፡ ጥናት ፡ እንዲያውሉ ፡ ያስችላቸዋል ።

(፰) <u>ሌሎች ፡ በፋኩልቲ ፡ አባሎች ፡ የተዘጋጁ ፡ ጽሑፎች</u> ፤ የፋኩልቲ ፡ አባ ሎች ፡ ሁሉ ፡ አድካሚ ፡ በሆነው ፡ የምርምር ፡ ፕሮግራም ፡ ተካፋይ ፡ ሁነዋል ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ ያልተጠቀሱት ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

ሀ) ፕሮፌሰር ፡ ክሸችኖቢች ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሐት ፡ ብዙ ፡ ጽሑ ፎች ፡ ከማበርከታቸውም ፡ በላይ ፡ ከፍትሐ ፡ ብሐር ፡ ሕግ ፤ ከሙል ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ ግዴታዎች ፡ ቁጥሮች ፡ በፈረንሣይኛው ፡ መሠረት ፡ የተ ሻሻለ ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ትርጉም ፡ አዘጋጅተዋል ። ይኸውም ፡ ትርጉም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ እላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ክፍል ፡ ለመረዳት ፡

በማየ ፣ የሚረዳ ፣ ሲሆን ፣ አሁን ፣ ተረቅቆ ፣ የሚገኘው ፣ የዚሁ ፣ ክፍል ፣ አስተያየት ፣ መግለጫ ፣ ተጨማሪ ፣ ይሆናል ።

(ለ) ሚስተር ፣ ፊሸር ፣ ደግሞ ፣ የኢትዮጵያን ፣ የወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሥነ ፣ ሥርዓት ፣ ሕግ ፣ ከሕንድ ፣ ሥነ ፣ ሥርዐት ፣ ጋር ፣ በማስተናበር ፣ የሚገናኙበትን ፣ ምንጭ ፣ የሚያብራራ ፣ ጽሑፍ ፣ አሳትመዋል ። ይኸውም ፣ <u>የኢትዮጵያ ፣ የወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ ሥነ ፣ ሥርዐት ፣ ምንጭ ፣ መጽሐፍ</u> ፣ ለተባለው ፣ መጽሐፋቸው ፣ የመጀመሪያው ፣ ክፍል ፣ ነው ።

ሐ) ዶክተር ፣ ቫንደርሊንደን ፣ "ላ ፣ ኖሲዮን ፣ ደ ፣ ኮድ ፣ አን ፣ ኤሮፓ ፣ ኦክሲዴንታል ፣ ዱዝ ፣ ዊትዬም ፣ ሲክል ፣ ኤስ ፣ ደ ፣ ደፊናሲዮን" ፣ በሚል ፣ አርዕስት ፣ የሚያዘጋጁትን ፣ መጽሕፍትና ፣ "አብስትራክት ፣ ዲ ፣ ላ ፣ ጁስቲስ ፣ ኢንዲጀን ፣ ኤን ፣ ፔይ ፣ ዘንድ ፣ ኤን ፣ ፲፱፻፷፮ ፣ ፲፱፻፷፯ ፣ ኤ ፣ ፲፱፻፷፰" ብለው ፣ የሰየሙትን ፣ ጽሑፍ ፣ ማዘጋጀት ፣ በቅርቡ ፣ ጨርሰዋል ። ለኢትዮጵያ ፣ የሕግ ፣ መጽሔትም ፣ "ዘ ፣ ሬሌቫንስ ፣ ኦቭ ፣ ዘ ፣ ስተዲ ፣ ኦቭ ፣ ሊጋል ፣ ሂስትሪ ፣ ፎር ፣ ቤተር ፣ አንደርስታንዲንግ ፣ ኦቭ ፣ ሞደርን ፣ ኢትዮፕያን ፣ ሎው" (ዘመናዊውን ፣ የኢትዮጵያን ፣ ሕግ ፣ በይበልጥ ፣ ለመረዳት ፣ የሕግን ፣ ታሪክ ፣ ማጥናት ፣ ተገቢ ፣ ስለመሆኑ) በሚል ፣ አርዕስት ፣ ጽሑፍ ፣ አዘጋጅተዋል ። እንደዚሁም ፣ "ኩተሜ ፣ ዱ ፣ ማኑኤል ፣ ኤ ፣ ጁሪስፕሩዳንስ ፣ ዱ ፣ ድሩዋ ፣ ዛንድ" ፣ የሚባለውን ፣ መጽሐፋቸውን ፣ ዝግጅት ፣ በማጠናቀቅ ፣ ላይ ፣ ናቸው ። ከዚህም ፣ በቀር ፣ ስለ ፣ ሁኔታው ፣ ከዚህ ፣ በታች ፣ የሚገለጸውን ፣ <u>የኢትዮጵያ ፣ የሕግ ፣ ቤት ፣ መዛግብት ፣ እቅድ</u> ፣ ጀምረዋል ።

(፮) <u>ያልታተሙ ፣ የምርምር ፣ ጽሑፎች ፤ የሕግ ፣ ቤት ፣ መዛግብት ፣ እቅድ ፤</u>
የሕግ ፣ ፋኩልቲ ፣ መምህራን ፣ የተመደበላቸውን ፣ የትምህርት ፣ ዐይነት ፣ ለማስተማር ፣ የሚረዱዋቸውን ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ ዐይነት ፣ ጽሑፎች ፣ በየበኩላቸው ፣ መሰብሰብ ፣ ነበረባቸው ። ብዙው ፣ የተሰበሰበው ፣ በአንቀጽ ፣ ሆነ ፣ ወይም ፣ በመጽሐፍ ፣ መልክ ፣ ታትሞ ፣ ሊወጣ ፣ አይችልም ፤ ሆኖም ፣ ለክፍል ፣ መነጋገሪያ ፣ መሠረት ፣ ሊሆን ፣ ይችላል ። የተሰበሰቡት ፣ መረጃዎች ፣ ማለት ፣ የባንክ ፣ ሥርዐት ፣ የታክስ ፣ ሁኔታ ፣ ሐብትን ፣ በሥራ ፣ ላይ ፣ የማዋል ፣ ድንጋጌ ፣ የባጀት ፣ ዝግጅት ፣ የፓርላሜንት ፣ ሥነ ፣ ሥርዐት ፣ ወዘተርፈ ፣ ምርምር ፣ ለሚያደርጉ ፣ ሰዎች ፣ በሚያመች ፣ አኳኋን ፣ ማውጫ ፣ ተበጅቶላቸው ፣ አዲስ ፣ በተቋቋመው ፣ በኢትዮጵያ ፣ የሕግ ፣ ቤት ፣ መዛግብት ፣ ውስጥ ፣ በሚገባ ፣ እንዲቀመጡ ፣ ተደርጕአል ። በዶክተር ፣ ቫንደርሊንደን ፣ የሚመራው ፣ ይኸ ፣ ቤት ፣ መዛግብት ፣ የኢትዮጵያ ፣ የሕግ ፣ ባህልን ፣ የሚመለከቱ ፣ ጽሑፎች ፣ አሰቃማጭም ፣ ነው ። ይኸም ፣ የጽሑፎች ፣ መሰብሰብና ፣ ማስተርጐም ፣ እንደዚሁም ፣ ለወደፊት ፣ የሕግ ፣ ምሁራን ፣ በሚገባ ፣ ጠብቆ ፣ ማቆየት ፣ ከፍተኛ ፣ ተግባር ፣ ነው ።

(፯) የተማሪዎች ፡ የክረምት ፡ ወራት ፡ ምርምር ፤ በረጅሙ ፡ የክረምት ፡ ወራት ፡ የረፍት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ተማሪዎቹን ፡ በምርምር ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ አሰማርቶ ፡ ነበር ። በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. የክረምት ፡ ወራት ፡ በፋኩልቲው ፡ መምህ ራን ፡ መሪነት ፡ ተማሪዎቹ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ በስተደቡብ ፡ መቶ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ያህል ፡ ርቆ ፡ በሚገኘው ፡ በጉራጌ ፡ ክፍለ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ በሚገኝ ፡ ሥፍራ ፡ የሙከራ ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ ጥናት ፡ አድርገው ፤ ለንብረት ፡ ትምህርት ፡ ማስተ ማሪያ ፡ የሚጠቅም ፡ መረጃ ፡ ለማግኘት ፡ ተችሎአል ። ሌሎች ፡ ተማሪዎች ፡ ደግሞ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕጎች ፡ (ኮዶች) ውስጥ ፡ በአማርኛውና ፡ በእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ መካከል ፡ የሚገኙትን ፡ ልዩነቶች ፡ እንዲለቅሙና ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ መምህራን ፡ ዘንድ ፡ በቋንቋ ፡ ምክንያት ፡ የሚገጥመውን ፡ ችግር ፡ ለማቃለል ፡ በማሰብ ፡ ከአማርኛም ፡ ብዙ ፡ የሕግ ፡ ጽሑፎችን ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ እንዲተ ረጉሙ ፡ ተደርጐ ፡ ነበር ። በ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ. ም. የክረምት ፡ ወራት ፡ ደግሞ ፡ በአ ዲስ ፡ አበባና ፡ በሌላም ፡ ሥፍራ ፡ በጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ባለፉት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ከተወሰኑ ፡ ፍርዶች ፡ መካከል ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑትን ፡ ፍርዶችን ፡ ለመምረጥ ፡ ይቻል ፡ ዘንድ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔዎችን ፡ የማቅረብ ፡ ፕሮግራም ፡ ተጀመረ ። ይኸንንም ፡ ሥራ ፡ የሥራ ፡ ጓደ ኛዬ ፡ ሚስተር ፡ ኪንድሬድ ፡ ይከታተሉት ፡ ነበር ። የተሰበሰቡትም ፡ ፍርዶች ፡ ሁሉ ፡ ተራ ፡ ቁጥርና ፡ መግለጫ ፡ ተሰጥቶአቸው ፡ በሕግ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ እንዲገኙ ፡ ተደርጎአል ። ከነዚህም ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ሆነው ፡ የሚገ ኙት ፡ በዚህ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ ታትመው ፡ እንዲወጡ ፡ ይደረጋል ።

ከዚህም ፡ ጥረት ፡ የተነሳ ፡ ብዙ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔዎች ፡ የሚገኙ ፡ የሆነ ፡ እን ደሆነ ፡ ምናልባት ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔዎች ፡ መግለጫ ፡ ሌላ ፡ የተለየ ፡ እትም ፡ ማውጣት ፡ ያስፈልግ ፡ ይሆናል ። የሕግ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍትን ፡ በከፍተኛ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔዎች ፡ ማበልጸግ ፡ እንዲቻል ፡ ጽሑፎችን ፡ በሚገባ ፡ ለመቅዳት ፡ የሚ ያስችል ፡ የማባዣ ፡ መኪና ፡ ተገዝቶአል ። ተማሪዎችም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የምርምር ፡ አቅድ ፡ ለፋኩልቲው ፡ አባሎች ፡ የግል ፡ ዕርዳታ ፡ በማድረግ ፡ ላይ ፡ ናቸው ። ይኸ ንንም ፡ የክረምት ፡ ወራት ፡ ከፍተኛ ፡ ተግባር ፡ ለሚፈጽሙት ፡ ተማሪዎች ፡ በመ ጠኑ ፡ ገንዘብ ፡ ይከፈላቸዋል ።

በፋኩልቲው ፡ መምህራን ፡ የቅርብ ፡ ተቆጣጣሪነት ፡ ቁጥራቸው ፡ ከሀያ ፡ አም ስት ፡ የበለጠ ፡ ተማሪዎች ፡ በዚሁ ፡ ተግባር ፡ ተካፋይ ፡ ሁነዋል ። በዚሁም ፡ ሙከራ ለመረዳት ፡ እንደተቻለው ፡ ሥራው ፡ ለተማሪዎቹ ፡ ተጨማሪ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ የሰጣቸው ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ አስፈላጊያቸው ፡ የሆነ ፡ ውን ፡ የገንዘብ ፡ ዕርዳታ ፡ ሊያስገኝላቸው ፡ ችሎአል ። ለወደፊትም ፡ በቂ ፡ ገንዘብ ፡ ካገኘን ፡ የክረምት ፡ ወራት ሥራን ፡ ከሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ፕሮግራም ፡ አንዳንዱ ፡ ለማድረግ ፡ እንደምን ችል ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ።

(፮) የክብር ፡ ቅንጅት ፤ በሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ውስጥ ፡ ከተደረጉት ፡ እድገቶች ፡ አንዱ ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ የክብር ፡ ቅንጅት ፡ መቆም ፡ ነው ። የተለየ ፡ ሙያቸው ፡ እንደሚጠይቀው ፡ ሁሉ ፡ ተማሪዎቻችን ፡ ሲፈጽም ፡ የሚገባውን ፡ የሙያ ፡ ዐመል ፡ (ጠባይ) የሚቆጣጠር ፡ ሕግ ፡ አውጥተው ፡ ከአንድ ፡ የፋኩልቲው ፡ መምህር ፡ ጋር ፡ በመረዳዳት ፡ አሥራ ፡ ላይ ፡ አውለውታል ። እኔም ፡ አሁንም ፡ ወደ ፊትም ፡ የምመኘውና ፡ የማምነው ፡ ይኸ ፡ አድራጉት ፡ በቅርቡ ፡ በሕግ ፡ ሙያተኛነት ፡ ተርታ ፡ ለሚሰለፉት ፡ ወጣቶች ፡ ዋጋ ፡ እንደሚሰጥ ፡ ነው ።

(፯) ስለ ፡ ሕግና ፡ ስለ ፡ ኢኮኖሚ ፡ በፋኩልቲው ፡ የተደረጉ ፡ የጥናት ፡ ጉባኤዎች ፤ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከንግድ ፡ ሥራ ፡ ኮሌጅ ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ በ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም. ውስጥ ፡ አሥር ፡ ተከታታይ ፡ የሕግና ፡ የኢኮኖሚ ፡ እድገት ፡ ጥናት ፡ ጉባኤዎች ፡ አድርጉአል ። የጥናቱም ፡ ጉባኤ ፡ መሠረታዊ ፡ ዓላማ ፡ የሁለቱ ፡ ፋኩልቲ ፡ አባሎችን ፡ ለዚህ ፡ ዐይነተኛ ፡ ተግባር ፡ ለማነቃቃትና ፡ በይበልጥም ፡ እንዲብራሩላቸው ፡ ለማድረግ ፡ ነበር ። የውጭ ፡ ተናጋሪዎች ፡ የሚበዙትም ፡ የመንግሥት ፡ ሹማምንትና ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ ዐዋቂዎች ፡ (ኤክስፔርቶች) የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ በየስብሰባው ፡ አንዳንድ ፡ መግለጫ ፡ እንዲሰጡ ፡ ተጠርተው ፡ አስተያየታቸውን ፡ ለጉባኤው ፡ ገልጸዋል ።

ከነዚህም ፡ ተናጋሪዎች ፡ ብዙ ፡ የንግድ ፡ አቋሞችን ፤ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ የፕላኒንግ ፡ ቦርድ ፡ አባሎችና ፡ የዩኒቨርስቲ ፡ መምህራንም ፡ ጭምር ፡ ነበሩ ።

ንግግሩንም ፡ ለመምራት ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ ልዩ ፡ ዐዋቂዎች ፡ ተገኝተዋል ። በብዙዎችም ፡ ስብሰባዎች ፡ ግልጽና ፡ ጠቃሚ ፡ ውይይት ፡ ተደርጉአል ። በነዚሁም ፡ ስብሰባዎች ፡ በሚከተሉት ፡ አርዕስቶች ፡ ጉዳዮች ፡ ንግግር ፡ ተደርጉአል ።

ሀ- ስለ ፡ ልማት ፡ ሕግና ፡ የኢኮኖሚ ፡ መሠረታዊ ፡ አቋም ፤
ለ- ሁለተኛው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ፕላን ፤
ሐ- የኢትዮጵያ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ ልማት ፤
መ- የኢትዮጵያ ፡ የሰው ፡ የሥራ ፡ ጉልበት ፡ ፍላጎት ፤
ሠ- ሀብትን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የማዋል ፡ ሕግና ፡ ለዚህ ፡ ተግባር ፡ የሚውል ፡ ገንዘብ ፡ የሚገኝባቸው ፡ ምንጮች ፤
ረ- በኢትዮጵያ ፡ የሚገኙ ፡ የአበዳሪ ፡ ድርጅቶች ፤
ሰ- በኢትዮጵያ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ስለማቋቋም ፡ ሕጋዊና ፡ የአፈጻጸም ፡ ችግሮች ፤

ሸ- የኢትዮጵያ ፡ የቀረጥ ፡ አሰባሰብ ፡ ዘዴ ፤

ቀ- በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግና ፡ በልማዳዊ ፡ ሕግም ፡ ጭምር ፡ የሚፈጠሩ ፡ የመሬት ፡ ሕግ ፡ ችግሮች ፡ እና ፡

በ- የሙያተኞች ፡ ሕግ ፡ ችግሮች ።

(፫) <u>በተማሪዎች ፡ የተደራጀ ፡ የሕግ ፡ ሸንጎ</u> ፤ ሚያዝያ ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፩፡ ዓ. ም. የሕግ ፡ ተማሪዎች፡ ማኅበር ፡ የሕግ፡ ሸንጎ፡ ኰሚቴ፡ እንዲቋቋም ፡ ፈቀደ ፤ ኮሚቴው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ቤተሰቦች ፡ የሚጠቅሙ ፡ ተከታታይ ፡ የንግግ ሮች ፡ ፕሮግራም ፡ እንዲያዘጋጅ ፡ ማኅበሩ ፡ አዘዘ ። ይኸን ፡ ዐይነቱም ፡ የትምህ ርት ፡ ሸንጎ ፡ በዩኒበርሲቲው ፡ ውስጥ ፡ በተማሪዎች ፡ ሲዘጋጅ ፡ ይኸ ፡ የመጀመ ሪያው ፡ ጊዜ ፡ ነበር ።

የማኅበሩ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ የሆኑት ፡ አቶ ፡ ከበደ ፡ ካሣ ፤ እንዲሁም ፡ አባሎቹ፡ አቶ ፡ ዓለሙ ፡ ደነቀው ፤ አቶ ፡ ግርማ ፡ ታደሰና ፡ አቶ፡ ፍሥሐ ፡ ባይህ ፡ፕሮግራሙን በቶሎ ፡ እንዲያዘጋጁ ፡ ተመረጡ ። በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥም ፡ ሦስት ፡ በጣም ፡የው መሩና ፡ የሕግ፡ ቀን ፡ ተብሎ፡ በተሰየመው ፡ በግንቦት፡ ፳፱ ፡ ቀን፡ ከፍተኛ ፡ አድና ቆትን ፡ በማግኘት፡ የተፈጸሙ ፡ የንግግር፡ ፕሮግራሞችን፡ አዘጋጁ ። ግንቦት፡ ፯፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ. ም. በዩኒቨርሲቲ ፡ ተማሪዎች ፡ ማረፊያ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የካሊ ፎርኒያ፡ ክፍለ ፡ አገር ፡ ( ስቴት ) የጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛ ፡ ስታንሊ ፡ ሞስክ ፡ ንግግር ፡ ያደረጉበት ፡ ሸንጎ ፡ ተደረገ ። ጀስቲስ ፡ ሞስክ ፡ በሔግ ፡ የሚገኘውን ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ፍትሕ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቅርቡ ፡ የጐበኙና ፡ በዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚታየው ፡ በደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ ላይ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በላይቤሪያ ፡ የቀረ በው ፡ ክስ ፡ ሲሰማ ፡ ጉዳዩን ፡ የተከታተሉ ፡ ናቸው ።

እርሳቸውም ፡ በንግግራቸው ፡ ውስጥ ፡ የዚህን ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ከፍተኛና ፡ አከራካሪ ፡ የሆነውን ፡ ክስ ፡ ሁኔታ ፡ ከመግለጻቸው ፡ በፊት ፡ የዚህን ፡ የዓለም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ታሪክና ፡ ሥራ ፡ በቅድሚያ ፡ ገለጹ ። በንግግራቸውም ፡ መደምደ ሚያ ፡ ላይ ፡ የዓለም ፡ ሰላምና ፡ ፍትሕ ፡ በሕግ ፡ አማካይነት ፡ እንዲጠበቅ ፡ ለማ ድረግ ፡ ይኸ ፡ የዓለም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊፈጽመው ፡ ስለሚገባው፡ ተግባርና ፡ ስለ ፡ ወደፊት ፡ ዕድሉም ፡ ለቀረቡላቸው ፡ ጥያቄዎች ፡ መልስ፡ ሰጥተዋል ።

ከሁለት ፡ ሳምንታት ፡ በኋላም ፡ በሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ውስጥ ፡ " በማደግ ፡ ላይ ፡ በሚገኙ ፡ አገሮች ፡ የፓርላማ ፡ ተግባር " በሚል ፡ አርዕሶት ፡ የሸንጎ ፡ ኰሚቴ ፡ አንድ ፡ የውይይት ፡ ፕሮግራም ፡ አበረከተ ።

በዚሁም ፡ ሸንጎ ፡ ላይ ፡ አፈ ፡ ጉባዔ ፡ የመሆንና ፡ የኢትዮጵያን ፡ ፓርላማም፡ ሕጋዊ ፡ አቋቋም ፡ የመግለጹ ፡ ዕድል ፡ ለኔ ፡ ተሰጥቶ ፡ ነበር ። የሕግ ፡ መምሪያ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ የተከበሩ ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ ግርማ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ፡ እርሳቸው ፡ የሚገኙበትን ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ስለሚመለከተው ፡ የፓርላማ ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም ፤ የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባል ፡ ( የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ተማሪ )

የሆኑት ፡ ሻሽራሻ ፡ ዘውዱ ፡ አቶር ፡ ደግሞ ፡ የሕግ ፡ መወሰኛን ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ተግባር ፡ በዝርዝር ፡ አስረድተዋል ። እንደዚሁም ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ተማሪ ፡ የሆኑትና ፡ በአለፈው ፡ የሕግ ፡ መምሪያ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ መማክርት ፡ ምርጫ ፡ በእጩነት ፡ የቀረቡት ፡ ወይዘሮ ፡ ያይኔ ፡ አበባ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የምርጫ ፡ ውድድርና ፡ አፈጻጸም ፡ ተናግረዋል ። የብዙ ፡ ጥያቄዎችም ፡ መሰንዘር ፡ ጥያቄና ፡ መልስ ፡ የመስጠቱ ፡ መሟሟቅ ፡ ፕሮግራሙን ፡ ከሁለት ፡ ሰዓት ፡ ለበለጠ ፡ ጊዜ ፡ እንዲራዘም ፡ አድርጎት ፡ ነበር ።

ግንቦት ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፭ ፡ ዓ. ም. የሸንጎ ፡ ኮሚቴ ፡ የ፲፱፻፷፮ ፡ ዓ. ም. ትምህርት ፡ ወቅት ፡ የመጨረሻ ፡ የሆነውን ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ያህል ፡ ሰዎች ፡ የተገኙበትን ፡ የመጨረሻ ፡ ፕሮግራሙን ፡ በራስ ፡ መኰንን ፡ አዳራሽ ፡ ውስጥ ፡ አቀረበ ። የፕሮግራሙም ፡ አርዕስት ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ መሻሻል ፤ በፓርላማ ፡ የሚገኘው ፡ የጭሰኝነት ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ የሚል ፡ ነበር ። የሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ የፋኩልቲው ፡ ተማሪዎች ፡ የጭሰኛን ፡ ችግር ፡ በንብረት ፡ ትምህርታቸው ፡ ተከታትለው ፡ ስለነበረ ፤ የሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ ተማሪ ፡ የነበረው ፡ አቶ ፡ ሰላሙ ፡ በቀለ ፡ የፕሮግራሙ ፡ አፈጉባዔ ፡ እንዲሆንና ፡ የጭሰኛ ፡ ሁኔታ ፡ መሻሻል ፡ የሚመለከቱትን ፡ ጊዜያዊ ፡ ችግሮች ፡ ውይይት ፡ እንዲደረግባቸው ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ተጠየቀ ። በዩኒቨርስቲ ፡ ኮሌጅ ፡ የጂኦግራፊ ፡ ክፍል ፡ ኃላፊ ፡ የሆኑት ፡ አቶ ፡ መስፍን ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ሲወራረቡ ፡ ስለመጡት ፡ ልማዶችና ፡ በኢትዮጵያ ፡ የእርሻ ፡ ሥራ ፡ መስፋፋት ፡ ላይ ፡ ስለሚያስከትሉት ፡ ችግሮች ፡ ተናገሩ ። ከእርሳቸውም ፡ ቀጥሎ ፤ በሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የንብረት ፡ ሕግ ፡ አስተማሪ ፡ የሆኑት ፡ ሚስተር ፡ አዌን ፡ ሲልኪ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚገኙት ፡ የመሬት ፡ ጭሰኝነት ፡ ሥርዐቶች ፡ ሁኔታ ፡ በአጭሩ ፡ ገለጹ ። በመጨረሻም ፡ የተከበሩ ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ ግርማ ፡ ወልደጊዮርጊስ ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ በፓርላማ ፡ ስለሚመከርበት ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ሁኔታና ፡ ለወደፊትም ፡ ሌላ ፡ ሕግ ፡ ሊወጣ ፡ ስለሚቻልበት ፡ አኳኋን ፡ ተናገሩ ።

የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ማኅበር ፡ የሸንጎ ፡ ኮሚቴ ፡ የዩኒቨርሲቲ ፡ ተማሪዎች ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እድገትና ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ አቋም ፡ በሚደረግ ፡ ውይይት ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑ ፡ አስተያየቶችን ፡ ሊያካፍሉ ፡ የሚችሉ ፡ መሆናቸውን ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ባዘጋጃቸው ፡ ሦስት ፡ ስብሰባዎች ፡ በሥራ ፡ ሊያሳይ ፡ ችሎአል ። ስለዚህ ፡ ላለፈው ፡ ድካማቸው ፡ ተማሪዎቹ ፡ ሊመሰገኑ ፡ ይገባል ። ይኸም ፡ የመልካም ፡ ሙያውጥን ፡ ዘላቂ ፡ እንዲሆን ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ።

(፬) ሌሎች ፡ እንግዶች ። በዚሁ ፡ ዓመት ፡ ፋኩልቲው ፡ በብዙ ፡ የታወቁ ፡ ሰዎች ፡ የመጐብኘት ፡ ዕድል ፡ ገጥሞታል ። ከዓለም ፡ የሙያተኞች ፡ ድርጅት ፡ የመጡት ፡ ዶክተር ፡ ሲ. ደብሊው. ጀንክስ ፡ በኛ ፡ ፋኩልቲ ፡ አማካይነት ፡ በኢንተርናሽናል ፡ ድርጅቶች ፡ የሕግ ፡ ተገቢ ፡ አፈጻጸም ፡ (ዲውፕሮሲስ ፡ ኦቭሎው) በሚል ፡ አርዕስት ፡ ንግግር ፡ አድርገዋል ።

እንደዚሁም ፡ የካርቱም ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ዲን ፡ ዛኪ ፡ ሙስጠፋ ፡ በሱዳን ፡ የሕግ ፡ እድገትና ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ ለተማሪዎቻችን ፡ ንግግር ፡ አድርገዋል ። የኢንተርናሽናል ፡ የሕግ ፡ ሊቆች ፡ ኮሚሽነር ፡ ዶክተር ፡ ሲን ፡ ማክብራይድ ፡ በቅርቡ ፡ ኮሚሲዮኑ ፡ በባንኮክ ፡ ስለአደረገው ፡ ስብሰባና ፡ በማደግ ፡ ላይ ፡ በሚገኙ ፡ አገሮች ፡ የሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ ድርሻ ፡ ተግባር ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ ንግግር ፡ አድርገዋል ።

ለጉብኝት ፡ የመጡ ፡ እንግዶች ፡ የሚቺጋኑ ፡ ዳኛ ፡ ቻርልስ ፡ ፋርመርና ፡ የሬዲንግ ፡ ዩኒቨርስቲው ፡ ፕሮፌሰር ፡ ኤም. ጂ. ሊሕማን ፡ በተገኙበት ፡ በመኖሪያ ፡ ቤቴ ፡ ከተማሪዎች ፡ ግማሾቹ ፡ በተገኙበት ፡ የመወያየት ፡ ስብሰባዎች ፡ ተደርገዋል ። ስለ ፡ አፍሪካ ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ድርጅቶችና ፡ የኢኮኖሚ ፡ እድገት ፡ በሚያደርጉት ፡ ምርምር ፡ ምክንያት ፡ የመጡት ፡ የሚቺጋን ፡ ዩኒቨርስቲው ፡ ፕሮፌሰር ፡ ደብሊው. ቢ. ሐርቤይ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤታችንን ፡ ጎብኝተዋል ። የካሊፎርኒያ ፡ ዩኒበርስቲው ፡ ፕሮፌሰር ፡ ኤም. ኤል. ሽዋርትዝ ፡ ለሁለት ፡ ሳምንት ፡ ያህል ፡ ጎብኝተውናል ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተገለጸውም ፡ ስለ ፡ ሥራችን ፡ አካሄድ ፡ አስተያየታቸውን ፡ ያስፈሩበት ፡ መግለጫ ፡ ለዩኒቨርስቲው I ለፎርድ ፡ ፋውንዴሽንና ፡ ለሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ቀርቦአል ።

(፩) ስለ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ። የሕግ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ በዝግታ ፡ በማደግ ፡ ላይ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ዓመት ፡ በቤተ ፡ መጻሕፍታችን ፡ የሚገኙት ፡ መጻሕፍት ፡ ብዛት ፡ ወደ ፡ ፯ሺህ ፡ እንደደረሰ ፡ ተገምቶአል ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የሙሉ ፡ ጊዜ ፡ የቤተ መጻሕፍት ፡ ኃላፊ ፡ ሠራተኛ ፡ አለን ። በቤተ ፡ መጻሕፍታችን ፡ የሕግ ፡ ሙያተኞች ፡ የመንግሥትና ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ሠራተኞች ፡ ይገለገሉበታል ። ቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ የሕግ ፡ ሞያ ፡ የሕግ ፡ ምርምር ፡ ምንጭ ፡ ሆኖ ፡ እንደሚገመት ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ። ቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ፍጹም ፡ አካል ፡ ነው ። ሳምንቱን ፡ በሙሉና ፡ በረጅሙ ፡ የእረፍት ፡ ጊዜም ፡ አዘውትሮ ፡ የሚሠራ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ነው ። በሰኔ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ በሕግ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ አማካሪያችን ፡ በፕሮፌሰር ፡ አልበርት ፡ ብሉሽቴን ፡ ጉብኝት ፡ ለመጠቀም ፡ ችለናል ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ወደፊት ፡ ልናደርገው ፡ የሚገባውን ፡ እድገት ፡ የሚያመለክት ፡ ሰሌዳ ፡ በማዘጋጀት ፡ ረድተውናል ። ፕሮፌሰር ፡ ብሉሽቴን ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍታችንን ፡ በማቋቋም ፡ ረገድ ፡ ለሁለት ፡ ዓመት ፡ በጣም ፡ ጠቃሚና ፡ አስፈላጊም ፡ የሆነ ፡ አገልግሎት ፡ ፈጽመዋል ። ቤተ ፡ መጻሕፍታችንን ፡ በዓለም ፡ አቀፍ ፡ ደረጃ ፡ ለማስገኘት ፡ በምናደርግበት ፡ ጊዜ ፡ እኚህ ፡ የታወቁ ፡ ሰው ፡ አገልግሎታቸውን ፡ እንዲቀጥሉልን ፡ የፎርድ ፡ ፋውንዴሽን ፡ ስለሚረዳን ፡ በጣም ፡ ዕድለኞች ፡ ነን ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ የአፍሪካ ፡ አንድነት ፡ ድርጅትና ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ የአፍሪካ ፡ ኢኮኖሚክ ፡ ኮሚሽን ፡ መንበር ፡ ናት ። አዲስ ፡ አበባ ፡ የኢንተርናሽናል ፡

ከተማ ፣ ናት ። ስለዚህ ፣ ጠቃሚ ፣ የሆኑትን ፣ የአፍሪካን ፣ የሕግ ፣ ጽሑፎች ፣ በብዛት ፣ መሰብሰብ ፣ አስፈላጊ ፣ መሆኑ ፣ ግልጽ ፣ ነው ። ይልቁንም ፣ የኢትዮጵያ ፣ የሕግ ፣ አመራር ፣ ከልዩ ፣ ልዩ ፣ ምንጭ ፣ የተውጣጣና ፣ በዓለም ፣ ከሚገኙ ፣ የሕግ ፣ ሐሳቦች ፣ ብዙዎችን ፣ የሚያጣምር ፣ በመሆኑ ፣ ከሲቢልና ፣ ከኮመንሎው ፣ ከሁቱም ፣ የሕግ ፣ ዐይነቶች ፣ መጻሕፍት ፣ በመሰብሰብ ፣ የተሟላ ፣ ቤተ ፣ መጻሕፍት ማቋቋም ፣ በጣም ፣ አስፈላጊ ፣ ነው ። በአጭሩ ፣ በአፍሪቃ ፣ በጣም ፣ ጥሩ ፣ የሆነ፣ ሕግ ፣ ቤተ ፣ መጻሕፍት ፣ ያስፈልገናል ፣ የገንዘብ ፣ ዕርዳታ ፣ በማግኘት ፣ ረገድ ፣ በመታደላችን ፣ የምንመኘው ፣ ቤተ ፣ መጻሕፍት ፣ እንደሚኖረን ፣ እተማመናለሁ ።

(፮) <u>የውጭ ፣ አገር ፣ ጉብኝት</u> ። በሚያዝያ ፣ ወር ፣ ከሥራ ፣ ጓደኞቹ ፣ ከፕሮፌሰር ፣ ጂ. ክሽችኖቢችና ፣ ከአቶ ፣ ነጋ ፣ ተሰማ ፣ ጋር ፣ ወደ ፣ ኢባዳን ፣ ናይጂሪያ፣ ሄደን ፣ ነበር ።

በአፍሪቃ ፣ ክፍለ ፣ ዓለም ፣ የሕግ ፣ ትምህርት ፣ ስለሚስፋፋበት ፣ ሁኔታ ፣ ለመነጋገር ፣ በተሰበሰቡበት ፣ የአፍሪቃ ፣ የሕግ ፣ መምህራን ፣ ስብሰባ ፣ ተካፋይ ፣ ሆነናል ። ጉባኤውም ፣ በተባበረ ፣ ድምጽ ፣ ከአጸደቃቸው ፣ ውሳኔዎች ፣ አንዱ ፣ በአፍሪቃ ፣ የሕግ ፣ መምህራን ፣ ማኅበር ፣ ተቋቁሞ ፣ ለወደፊቱ ፣ ስብሰባዎችን ፣ እንዲያዘጋጅና ፣ በልዩ ፣ ልዩ ፣ የአፍሪቃ ፣ የሕግ ፣ ትምህርት ፣ ቤቶች ፣ መካከል ፣ በጣም፣ ተፈላጊ ፣ የሆነውን ፣ የሐሳብ ፣ መለዋወጥ ፣ እንዲኖር ፣ እንዲያደርግ ፣ የቀረበው፣ ሐሳብ ፣ ነው ።

በግንቦት ፣ ወር ፣ ደግሞ፣ ከአርት፣ ፋኩልቲው ፣ ዲን፣ ከዶክተር ፣ አብርሃም ፣ ደምዝ ፣ ጋር ፣ በሴኔጋል ፣ ወደሚገኘው ፣ የዳካር ፣ ዩኒበርስቲ ፣ ሄደን ፣ በአፍሪቃ፣ በሚገኙ ፣ የእንግሊዘኛና ፣ የፈረንሣይኛ ፣ ቋንቋ ፣ ተናጋሪ ፣ ዩኒበርሲቲዎች ፣ መካከል ፣ ስለሚኖረው ፣ መተባበር ፣ በተደረገው ፣ ንግግር ፣ ተካፋይ ፣ ሆነናል። በዚሁም ፣ ጊዜ ፣ በዳካር ፣ ከሚገኘው ፣ የሕግ ፣ ፋኩልቲ ፣ ዲን ፣ ጋር ፣ ተገናኝተን፣ የቤተ መጻሕፍት ፣ ዕቅድ ፣ ከማዘጋጀታችንም ፣ ሌላ ፣ ስለ ፣ መጻሕፍትና ፣ ተስፋም ፣ እንደሚደርገው ፣ መምህራንን ፣ ስለመለዋወጥ፣ ለመነጋገር ፣ ዕድል ፣ አግኝቼ ፣ ነበር ።

በረጅም ፣ የእረፍት ፣ ጊዜ ፣ አቶ ፣ ሰላሙ ፣ በቀለና ፣ አቶ ፣ ፋሲል ፣ ናሆም ፣ የተባሉት ፣ ሁለት ፣ ተማሪዎቻችን ፣ የጐረቤት ፣ አገሮችን ፣ የዩኒቨርስቲ ፣ የሕግ ፣ ትምህርት ፣ ቤቶች ፣ ጐብኝተዋል ። አቶ ፣ ፋሲል ፣ በካርቱም ፣ ዩኒቨርስቲ ፣ አቶ ፣ ሰላሙ ፣ ደግሞ ፣ በዳሬሰላም ፣ በምሥራቅ ፣ አፍሪቃ ፣ ዩኒቨርስቲ ፣ የሕግ ፣ ፋኩልቲ፣ ገብተው ፣ ትምህርቱን ፣ ተከታትለዋል ። ለወደፊትም ፣ ይኸን ፣ ዐይነቱ ፣ መለዋወጥ ፣ እንደሚቀጥል ፣ ተስፋ ፣ አደርጋለሁ ።

## ማጠቃለያ ።

በመጨረሻም ፡ ለፎርድ ፡ ፋውንዴሽን ፤ ለኒው ፡ ዎርልድ ፡ ፋውንዴሽንና ፡ ለሌሎችም ፡ የግል ፡ በጎ ፡ አድራጊዎች ፤ ለሕግ ፡ መጽሔት ፡ ጠባቂዎችና ፡ ደጋፊዎች ፤ ለታላቋ ፡ ብሪታንያ ፤ ለቤልጂክ ፤ ለፈረንሳይ ፤ ለሕንድና ፡ ለዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ መንግሥታት ፡ ለሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ ስለሰጡት ፡ ዕርዳታ ፡ ምስጋናችንን ፡ ልገልጽ ፡ እወዳለሁ ።

በዩኒቨርስቲው ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ውስጥ ፡ በየጊዜው ፡ የትንንሹ ፡ አቤቱታ ፡ መሰንዘሪያ ፡ ኢላማ ፡ የሆነውን ፡ የዩኒቨርስቲውን ፡ አስተዳደር ፡ ሳይጠቅሱ ፡ ማለፍ ፡ ተገቢ ፡ አይሆንም ። በነዚህ ፡ በመቋቋሚያው ፡ የመጀመሪያ ፡ ዓመታት ፡ የዚህን ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ መሪዎች ፡ የሚገጥማቸውን ፡ ብርቱ ፡ ተግባር ፡ ወደመርሳት ፡ የምናዘነብል ፡ ይመስለኛል ። በዚህ ፡ ፋኩልቲ ፡ ላይ ፡ እስካሁን ፡ ስለተጣለው ፡ አደራና ፡ እምነት ፡ በእርግጥ ፡ አደንቃለሁ ። የሥራ ፡ ጓደኞቼም ፡ በበኩላቸው ፡ ፕሮግራማችንን ፡ ለማቃናትና ፡ በትጋት ፡ ለመምራት ፡ ተባብረው ፡ ይሠራሉ ። ስለዚህ ፡ የዲኑ ፡ ተግባር ፡ የቀለለ ፡ ሆኖአል ። በመጨረሻም ፡ ተማሪዎቹ ፡ በብዙ ፡ አስፈላጊ ፡ ምክንያቶች ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ እራሱ ፡ ናቸው ። የሥራ ፡ ባልደረቦችና ፡ እኔም ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ከሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ እንደምንሠራ ፡ እናምናለን ። በዚህም ፡ መንፈስ ፡ ለነዚህ ፡ የሕግ ፡ ባለሙያዎች ፡ ሰላምታችንን ፡ እናቀርብላቸዋለን ።

## በሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ተማሪዎች ፡ የ፲፱፻፶፯—፲፱፻፶፰ ዓ. ም. ።

### በሕግ ፡ የኤል. ኤል. ቢ. ዲግሪ ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. አግኝተው ፡ የሚመረቁ ፡ የሙሉ ፡ ቀን ፡ ተማሪዎች ።

ሚስ ፡ አሌክሳንድራ ፡ ሐማዊ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ማሞ ፡ መዘምር ፡
አቶ ፡ ሥሑል ፡ ሚካኤል ፡
አቶ ፡ ሰላሙ ፡ በቀለ ፡
አቶ ፡ ሽመልስ ፡ ሑሴን ፡
የሻምበል ፡ ቀነዓ ፡ ጉማ ፡
አቶ ፡ ኃይለ ፡ ሚካኤል ፡ ከበደ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ አበራ ፡ ባንቲዋሉ ፡
የሻምበል ፡ አበበ ፡ ጓንጉል ፡
አቶ ፡ አባቢያ ፡ አባጆቢር ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ኢያሱ ፡ አያል ፡
አቶ ፡ ዘርዓ ፡ ብሩክ ፡ አበራ ፡
አቶ ፡ ያዕቆብ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ ዮሐንስ ፡ ጎሩይ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ዳንኤል ፡ ዘለቀ ፡
አቶ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ አረጋይ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ጌታሁን ፡ ዳምጤ ፡
አቶ ፡ ግርማ ፡ ታደሰ ፡

### በሕግ ፡ የኤል. ኤል. ቢ. ዲግሪ ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. አግኝተው ፡ የሚመረቁ ፡ የሙሉ ፡ ቀን ፡ ተማሪዎች ።

የመቶ ፡ አለቃ ፡ መስፍን፡ ገብረ ቃል ፡
አቶ ፡ ሠመረ ፡ አብ ፡ ሚካኤል ፡
የመቶ ፡ አለቃ፡ ሽመልስ፡ መታፈሪያ ፡
አቶ ፡ በቀለ ፡ ወልዴ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ብርሃኑ ፡ ባይሀ ፡
አቶ ፡ ተክሉ ፡ መኮንን ፡
አቶ ፡ ታየ ፡ ንጋቱ ፡
የሻምበል ፡ ታደሰ ፡ አብዲ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ጉርሙ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ኃይሉ ፡ መኮንን ፡
አቶ ፡ አበበ ፡ ወርቄ ፡
አቶ ፡ ከበደ ፡ ካሳ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ወንዳየን ፡ ምሕረቱ ፡
አቶ ፡ ዓለሙ ፡ ደነቀው ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ዓለማየሁ ፡ አሰፋው ፡
አቶ ፡ ዘመነ ፡ ካሴኝ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ዘርአይ፡ ሀብተ፡ ሥላሴ፡
አቶ ፡ ዘገየ ፡ አሰፋው ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ይልማ ፡ ግዛው ፡
አቶ ፡ ጠዓመ ፡ በየነ ፡
አቶ ፡ ጥኡመልሳን ፡ ለማ ፡
አቶ ፡ ፋሲል ፡ ናሆም ፡
አቶ ፡ ከስተ ፡ ኃይሌ ፡
አቶ ፡ ፍሥሐ ፡ ባይሀ ፡

### በሕግ ፡ የኤል. ኤል. ቢ. ዲግሪ ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. አግኝተው የሚመረቁ ፡ የግማሽ ፡ ቀን ፡ (የማታ ፡ ተማሪዎች) ።

አቶ ፡ መብራህቱ ፡ ዮሐንስ ፡
አቶ ፡ መንገሻ ፡ ወርቅነህ ፡
አቶ ፡ መኰንን ፡ እውነቱ ፡
አቶ ፡ ሰይፉ ፡ ፈለቀ ፡
ሚስተር ፡ አር. ኤች. አር. ራጂያ ፡
አቶ ፡ በቀለ ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል ፡
አቶ ፡ ቡልቻ ፡ ደመቅሣ ፡
አቶ ፡ ነቢየ ፡ ልዑል ፡ ክፍሌ ፡
አቶ ፡ ነጋ ፡ ፋንታ ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ ጸጋዬ ፡

አቶ ፡ አበራ ፡ ጀምበሬ ፡
አቶ ፡ እያሌው ፡ ዘለቀ ፡
አቶ ፡ እጅጉ ፡ ደምሴ ፡
አቶ ፡ ክበደ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ ካሣ ፡ በየነ ፡ አየለ ፡
አቶ ፡ ወርቁ ፡ ተፈራ ፡
አቶ ፡ ዓቢዮ ፡ ገለታ ፡

## በሕግ ፡ ዲፕሎማ ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. አግኝተው ፡ የሚመረቁ ፡ ተማሪዎች ።

አቶ ፡ መስፍን ፡ አምባቸው ፡
አቶ ፡ መስፍን ፡ ፋንታ ፡
አቶ ፡ መንክር ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ መንግሥቱ ፡ እምሩ ፡
አቶ ፡ መንግሥቱ ፡ ወልደ ፡ አረጋይ ፡
አቶ ፡ ሙሉቱ ፡ ልካሳ ፡
አቶ ፡ ምናሴ ፡ ደጉ ፡
አቶ ፡ ሠይፉ ፡ ፈይሣ ፡
አቶ ፡ ሰይፉ ፡ አናጌ ፡
አቶ ፡ ሰይፉ ፡ የተሻ ፡ ወርቅ ፡
አቶ ፡ ሳሙኤል ፡ ወርቅነህ ፡
ሚስተር ፡ ሳካጂያን ፡ አራኪል ፡
አቶ ፡ በቀለ ፡ ተስፋዬ ፡
አቶ ፡ ብርሃኑ ፡ ሣህለ ፡ ጊዮርጊስ ፡
አቶ ፡ ብርሃኑ ፡ ክፈተው ፡
አቶ ፡ ተስፋዬ ፡ ሣህሌ ፡
አቶ ፡ ተስፋየ ፡ ዓለሙ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ተሾመ ፡ በየነ ፡
አቶ ፡ ተሾመ ፡ ገ. ሥላሴ ፡
የሻምበል ፡ ታምሩ ፡ ኃይለ ፡ ገብርኤል ፡
አቶ ፡ ታረቀኝ ፡ ኃይለ ፡ ልዑል ፡
የሻምበል ፡ ታዬ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡
አቶ ፡ ታዬ ፡ ወንድማገኘሁ ፡
አቶ ፡ ኃይሉ ፡ ወልደሚካኤል ፡
አቶ ፡ ኃይሌ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ነጋሽ ፡ ተክለ ፡ ማር
ያም ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ በቀለ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ አሰፋ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ አበራ ፡ ጉበና ፡
አቶ ፡ አብርሃም ፡ ጺጋዬ ፡
ሚስስ ፡ ማሪካ ፡ አርቫኒቶፖ ፡
አቶ ፡ አክሊሉ ፡ አጥላባቸው ፡
አቶ ፡ አክሊሉ ፡ ቤተ ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ አድነው ፡ ኃይለ ፡ ሚካኤል ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ እርጸው ፡ ዳርጌ ፡
የሻምበል ፡ ካሣዬ ፡ ማንደፍሮህ ፡
አቶ ፡ ካሣዬ ፡ አደም ፡
አቶ ፡ ከፈለኝ ፡ ማንያዝሃል ፡
የሻምበል ፡ ወልደ ፡ ሐዋርያት ፡ ገብረ ፡
ማርያም ፡
ሻምበል ፡ ዘውዴ ፡ ኦቶሮ ፡
የሻለቃ ፡ ይልማ ፡ ወልደሰማያት ፡
አቶ ፡ ደምሴ ፡ በቀለ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ዳምጠው ፡ ምንልኬ ፡
አቶ ፡ ጀማነህ ፡ መኳሻ ፡
ሚስተር ፡ ጆዋኪም ፡ ማቶቩ ፡
አቶ ፡ ጆሴፍ ፡ ኃይሌ ፡
አቶ ፡ ገብረየሱስ ፡ ኃይለማርያም ፡
አቶ ፡ ጉደታ ፡ ቦሩ ፡
የሻምበል ፡ ጌታሁን ፡ በቀለ ፡
አቶ ፡ ግርማ ፡ ደሳለኝ ፡
አቶ ፡ ግርማይ ፡ ዘወልደ ፡
አቶ ፡ ጸደቀ ፡ ተክሌ ፡

## በሕግ ፡ ሠርቲፊኬት ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. አግኝተው ፡
## መረቁ ፡ ተማሪዎች ።

አቶ ፡ ሰማ ፡ ሐጐስ ፡
አቶ ፡ ሰማ ፡ ወልደሰማዕት ፡
አቶ ፡ ለገሠ ፡ አበበ ፡
መዘምር ፡ መልከጼዴቅ ፡ ወልደሥላሴ ፡
አቶ ፡ መብራቴ ፡ ጉባ
አቶ ፡ መኰንን ፡ አጐናፍር ፡
አቶ ፡ መኰንን ፡ ወልደማርያም ፡
አቶ ፡ መጨጊያ ፡ ቢራቱ ፡
አቶ ፡ ሙሉጌታ ፡ ሀብተገብርኤል ፡
አቶ ፡ ሙሉጌታ ፡ መኰንን ፡
አቶ ፡ ሙሉጌታ ፡ በሪሁን ፡
የሻለቃ ፡ ሙሉጌታ ፡ እንዳይላሉ ፡
ሌተና ፡ ኰሎኔል ፡ ምሕረት ፡ ገብረ ፡
ሰላም ፡
አቶ ፡ ሰይፉ ፡ አስረስ ፡
አቶ ፡ ሱልጣን ፡ ሰይድ ፡
አቶ ፡ ሸዋንግዛው ፡ ወልደዮሐንስ ፡
አቶ ፡ ሸዋየ ፡ ሰማ ፡
አቶ ፡ ሽመልስ ፡ ተፈራ ፡
አቶ ፡ በቀለ ፡ አብቤ ፡
አቶ ፡ በቀለ ፡ ገድሌ ፡
አቶ ፡ ብርሃነመስቀል ፡ ጸጋየ ፡
የሻምበል ፡ ብርሃኔ ፡ ንጋቱ ፡
አቶ ፡ ብዙአየን ፡ ህዱግ ፡
አቶ ፡ ተረፈ ፡ ገሠሠ ፡
የሻምበል ፡ ተሰፋዬ ፡ መንገሻ ፡
አቶ ፡ ተፈራ ፡ ደነቀ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ሐጐስ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡
የሻምበል ፡ ታደሰ ፡ እንግዳ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ወልደመስቀል ፡
አቶ ፡ ኃይለማርያም ፡ ተሰፋት ፡
አቶ ፡ ኃይለማርያም ፡ ገመዳ ፡

አቶ ፡ ኃይሉ ፡ በየነ ፡
አቶ ፡ ነጋ ፡ ቢሰጥ ፡
አቶ ፡ ነጋሽ ፡ ተክለማርያም ፡
አቶ ፡ ንጉሤ ፡ ነውጤ ፡
አቶ ፡ ንጉሤ ፡ አበበ ፡
አቶ ፡ አማረ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
አቶ ፡ አሥራት ፡ ለገሠ ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ ሀብቱ ፡ ማርያም ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ አሰፋ ፡ መንገሻ ፡
አቶ ፡ አበበ ፡ ቦርሺ ፡
ያምባ ፡ አለቃ ፡ አበበ ፡ ወልደ ጊዮርጊስ
አቶ ፡ አባተ ፡ ስመኝ ፡
ፊታውራሪ ፡ አባይነህ ፡ ፊና ፡
አቶ ፡ አክሊሉ ፡ ተፈራ ፡
አቶ ፡ አየነው ፡ ወልደማርያም ፡
አቶ ፡ አድማሱ ፡ እውነቱ ፡
አቶ ፡ እሸቴ ፡ ደምቤ ፡
አቶ ፡ እንዳለ ፡ ወልደሚካኤል ፡
አቶ ፡ አላና ፡ በቲ ፡
አቶ ፡ ከበደ ፡ ቸኰል ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ከተማ ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ ከፋለ ፡ ወልደማርያም ፡
ግራዝማች ፡ ካሣ ፡ አበራ ፡
አቶ ፡ ክፍሌ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡
አቶ ፡ ወልደሙሴ ፡ ይህደጎ ፡
አቶ ፡ ወልደሚካኤል ፡ ገብረአብ ፡
የአሥር ፡ አለቃ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ደበላ ፡
አቶ ፡ ወልዴ ፡ ደምሴ ፡
አቶ ፡ ዋለልኝ ፡ መራ ፡
አቶ ፡ ዓለሙ ፡ መለሠ ፡
የሻለቃ ፡ ባሻ ፡ ዘውዴ ፡ ኃይሌ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ይልማ ፡ መንግሥቱ ፡
አቶ ፡ ይልማ ፡ ታደሰ ፡

አቶ ፡ ደርብ ፡ ቡታ ፡
አቶ ፡ ገብረመስቀል ፡ ካህሣይ ፡
አቶ ፡ ገብረማርያም ፡ መርጊያ ፡
አቶ ፡ ገብረማርያም ፡ እምባዩ ፡
አቶ ፡ ገዛኸኝ ፡ ወልዴ ፡
አቶ ፡ ጌታሁን ፡ ወልደሰንበት ፡
አቶ ፡ ጌታቸው ፡ ምንልክአለው ፡

አቶ ፡ ጌታቸው ፡ አሰፋው ፡
አቶ ፡ ግርማ ፡ አበበ ፡
አቶ ፡ ግዛው ፡ ብዛኔ ፡
አቶ ፡ ጉማዩ ፡ ዘመድኩን ፡
አቶ ፡ ጉይቶም ፡ በይን ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ፈቃዱ ፡ ዋኬኔ ፡

## <u>በሕግ ሠርቲፊኬት ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፰ ዓ. ም. አግኝተው ፡</u>
## <u>የሚመረቁ ፡ ተማሪዎች ።</u>
## <u>( አዲስ ፡ አበባ ፡ ክፍል «ሀ» ) ።</u>

አቶ ፡ ሰማ ፡ ደገፉ ፡
ሌ/ኰ መርድ ፡ አሰፋው ፡
አቶ ፡ መቆያ ፡ እሼቴ ፡
አቶ ፡ መኰንን ፡ አሰፋው ፡
አቶ ፡ ሙሉጌታ ፡ ይመኑ ፡
አቶ ፡ ምስጋና ፡ ታረቀኝ ፡
መምሬ ፡ ሣህለድንግል ፡ ገብረክርስቶስ
አቶ ፡ ሰሎሞን ፡ ዳኛቸው ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ሰብስቤ ፡ ከበደ ፡
አቶ ፡ ሰዋሰው ፡ እንየው ፡
አቶ ፡ ስለሺ ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ በላይ ፡ ጌታሁን ፡
አቶ ፡ በቀለ ፡ ወልደዮሐንስ ፡
ሌ/ኰ/ በየነ ፡ ዘአማኑኤል ፡
አቶ ፡ ተሰፋዬ ፡ በዛብህ ፡
አቶ ፡ ተሾመ ፡ ገላገል ፡
አቶ ፡ ተካ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡
አቶ ፡ ተፈራ ፡ በየነ ፡
የሻለቃ ፡ ታምራት ፡ ጉበዜ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ አብተው ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ወልደኪዳን ፡
አቶ ፡ ቴዎድሮስ ፡ አረፈ ፡ ዓይኔ ፡
አቶ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሐጉስ ፡
አቶ ፡ ኃይለሥላሴ ፡ በዛብህ ፡

የሻምበል ፡ ኃይሉ ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ ኃይሌ ፡ ወልደ ፡ ሐና ፡
አቶ ፡ ንጋቱ ፡ ሀብተማርያም ፡
የሻምበል ፡ አግረ ፡ አደራ ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ ተገኝ ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ አካለ ፡ ሕይወት ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ አየለ ፡
አቶ ፡ አሰፋው ፡ ይትባረክ ፡
አቶ ፡ አሰቤ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡
አቶ ፡ አሻግሬ ፡ ኃይሌ ፡
አቶ ፡ አበበ ፡ አውግቸው ፡
አቶ ፡ አብርሃም ፡ ተክሌ ፡
አቶ ፡ አብርሃም ፡ ድሬሳ ፡
አቶ ፡ አንዱ ፡ ዓለም ፡ በላይ ፡
አቶ ፡ አየለ ፡ ወልደሐዋርያት ፡
አቶ ፡ ኢያሱው ፡ ደስታ፡
አቶ ፡ እሼቴ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ እንዳለው ፡ መንገሻ ፡
አቶ ፡ እንግዳ ፡ ጌዋ ፡ ወርቁ ፡
የሻምበል ፡ ከበደ ፡ ሰንበቶ ፡
አቶ ፡ ካሣሁን ፡ አበበ ፡
አቶ ፡ ወርቁ ፡ ወልደ ፡ አረጋይ ፡
የሻለቃ ፡ ወንድሙ ፡ ገብረ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ ውቤ ፡ ወልደየስ ፡

የሻለቃ ፡ ዘሪሁን ፡ ገብረሥላሴ ፡
አቶ ፡ ዘውዴ ፡ መዝገቡ ፡
አቶ ፡ ዘውዴ ፡ ተድላ ፡
አቶ ፡ የማነብርሃን ፡ ወንድምአየሁ ፡
የሻለቃ ፡ የኔነህ ፡ ዓለሙ ፡
አቶ ፡ ደሳለኝ ፡ ዓለሙ ፡
ሴ/ኮ/ ደባልቄ ፡ ገዳ ፡
አቶ ፡ ጥላሁን ፡ ኃይሌ ፡
አቶ ፡ ጥላሁን ፡ እሸፋው ፡
አቶ ፡ ጸጊ ፡ ደርሰህ ፡
አቶ ፡ ፈለቀ ፡ ደምሴ ፡
አቶ ፡ ፍሬ ፡ ሕይወት ፡ በይበይን ፡

## በሕግ ፡ ሠርቲፊኬት ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፰ ዓ. ም. አግኝተው ፡

## የሚመረቁ ፡ ተማሪዎች ።

### (አዲስ ፡ አበባ ፡ ክፍል ፡ «ለ») ።

አቶ ፡ ለማ ፡ ተረፈ ፡
ሌ/ኮ ሉልሰገድ ፡ ኃይሌ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ሉልሰገድ ፡ ንጉሤ ፡
የሻምበል ፡ መለሰ ፡ መቼሳ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ መለሰ ፡ ዓለሙ ፡
ሐጂ ፡ መሐመድ ፡ ሲራጅ ፡
አቶ ፡ መስፍን ፡ ማሞ ፡
አቶ ፡ መስፍን ፡ ተፈራ ፡
አቶ ፡ መርጋ ፡ ሰኝ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ መንገሻ ፡ ዘውዴ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ መንግሥቱ ፡ በጋሻው ፡
አቶ ፡ ሙሉጌታ ፡ እንዳለ ፡
አቶ ፡ ማሙዬ ፡ መሸሻ ፡
አቶ ፡ ማሞ ፡ ወልደማርያም ፡
የአሥር ፡ አለቃ ፡ ምንይል ፡ ሸዋ ፡
ሀብቴ ፡
አቶ ፡ ሞቢሳ ፡ ጋሪ ፡
አቶ ፡ ሰይፉ ፡ ቦጂያ ፡
አቶ ፡ ሥዩም ፡ ኃይለሚካኤል ፡
አቶ ፡ ሥዩም ፡ አበበ ፡
አቶ ፡ ማህሌ ፡ ምሕረቱ ፡
አቶ ፡ ሽፈራው ፡ መሸሻ ፡
አቶ ፡ በቀለ ፡ ደምሴ ፡
አቶ ፡ ብርሃኑ ፡ አባይ ፡
አቶ ፡ ብርቁ ፡ አባሠራን ፡
አቶ ፡ ተስፋዬ ፡ ዱባለ ፡
አቶ ፡ ተረፈ ፡ ገብረመስቀል ፡
አቶ ፡ ተሾመ ፡ ቢረሳው ፡
አቶ ፡ ተሾመ ፡ ተሰማ ፡
አቶ ፡ ተሾመ ፡ ደምሴ ፡
አቶ ፡ ተከስተ ፡ ብርሃን ፡ ድባቡ ፡
ኰሎኔል ፡ ተክለማርያም ፡ አባይሬ ፡
አቶ ፡ ተክሌ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡
አቶ ፡ ተገኝ ፡ ሀብቴ ፡
አቶ ፡ ተገኝ ፡ ወንዳፍራሽ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ታዬ ፡ ቁምላቸው ፡
የሻምበል ፡ ታደሰ ፡ ተበፋ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ አበበ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ወልደጻድቅ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ጭጭ ፡ አይበሉ ፡
ያምሳ ፡ አለቃ ፡ ታደሰ ፡ ፈይሳ ፡
አቶ ፡ ኃይሉ ፡ ልዑል ፡ ሀብተዮሐንስ ፡
አቶ ፡ ኃይሉ ፡ ሥላሴ ፡ እሸፋው ፡
አቶ ፡ ኃይሉ ፡ ኢየሱስ ፡ ሙላት ፡
አቶ ፡ ኃይሌ ፡ እንዳፍር ፡
ሌ/ኮ አህመድ ፡ አሚኑ ፡
አቶ ፡ አለነ ፡ ወንዴ ፡

የሻምበል ፡ አማረ ፡ ንጋቱ ፡
አቶ ፡ አማረ ፡ ደግፌ ፡
አቶ ፡ አራጋው ፡ ወልዴ ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ ዘአማኑኤል ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ አሰፋው ፡ መሸሻ ፡
አቶ ፡ አሰፋው ፡ ገብረኢየሱስ ፡
አቶ ፡ አበበ ፡ ተሰማ ፡
አቶ ፡ አበበ ፡ አስገልጥ ፡
አቶ ፡ አድማሱ ፡ አስረስ ፡
የሻለቃ፡ አድማሱ ፡ ጀምበሬ ፡
አቶ ፡ አድማሴ ፡ ገሠሠ ፡
ወይዘሮ ፡ ዓይኔ ፡ አበባ፡ ሸዋንግዥው ፡
አቶ ፡ አጋ ፡ ነጋሽ ።
አቶ ፡ እሼቴ ፡ ከበደ ፡
አቶ ፡ ከበደ ፡ ተረፈ ፡
መቶ ፡ አለቃ ፡ ከፋለ ፡ አድገህ ፡
አቶ ፡ ካሳሁን ፡ ወርቅነህ ፡
አቶ ፡ ወልደትንሣኤ ፡ ገብረሚካኤል ፡
አቶ ፡ ወልደጻድቅ ፡ ወልደሰማዕት ፡
አቶ ፡ ወንድሙ ፡ ገብረመድኅን ፡
አቶ ፡ ወንድወሰን ፡ በቀለ ፡
አቶ ፡ ዓለማየሁ ፡ አጋ ፡
አቶ ፡ ዓለማየሁ ፡ ወንድሙ ፡
አቶ ፡ ዓለምሰገድ ፡ አርአያ ፡
አቶ ፡ ዕጹብ ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ የማነ ፡ ብርሃን ፡ መላኩ ፡
አቶ ፡ ይልማ ፡ በቀለ ፡
አቶ ፡ ይትባረክ ፡ ተሾመ ፡
አቶ ዲሚጥሮስ ፡ ገብረሐና ፡
አቶ ፡ ዳባ ፡ ሱንጣ ፡
አቶ ፡ ጌላሁን ፡ አባተ ፡
አቶ ፡ ገመቹ ፡ ጉታ ፡
አቶ ፡ ገብረሥላሴ ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ ፈንታሁን ፡ ብርሃኑ ፡
አቶ ፡ ፍታወቅ ፡ ደመኢየሱስ ፡

በሕግ ፡ ሠርቲፊኬት ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. ያገኙ ፡

የሚመረቁ ፡ ተማሪዎች ።

(አሥመራ) ።

አቶ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ ደባስ ፡
አቶ ሐሚድ ፡ ዑስማን ፡ እድሪስ ፡
አቶ ፡ ሑሴን ፡ ፋራሕ ፡
አቶ ፡ መሐመድ ፡ ሐንኪል ፡
አቶ ፡ መሐመድ ፡ ኑር ፡ ቁስማላ ፡
አቶ ፡ መሐመድ ፡ አሊ ፡ ሐሰን ፡
አቶ ፡ መሐመድ ፡ ኢብራሂም ፡ ሐንጋላይ
አቶ ፡ መሐመድ ፡ ኢድሪስ ፡ ዑመር ፡
አቶ ፡ መኰንን ፡ አስረሱ ፡
አቶ ፡ መኰንን ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ መዋእል ፡ መብራህቱ ፡
አቶ ፡ ሰሎሞን ፡ ኪሕሳይ ፡
አቶ ፡ ሰይድ ፡ ሐሊፋ ፡
አቶ ፡ ሰይድ ፡ ከሊፋ ፡
አቶ ፡ ሳልሕ ፡ ሺፋ ፡
አቶ ፡ ሥዩም ፡ ይሕደጐ ፡
አቶ ፡ ሥዩም ፡ ፍስሐ ፡ ጸዮን ፡
አቶ ፡ በየነ ፡ አስፍሐ ፡
አቶ ፡ በየነ ፡ ገብረሥላሴ ፡
አቶ ፡ ብርሃኔ ፡ ክፍለማርያም ፡
አቶ ፡ ተስፋይ ፡ ዘሚካኤል ፡
አቶ ተስፋ ፡ ጸዮን ፡ ኢያሱ ፡
አቶ ፡ ተክሌ ፡ ገብረክርስቶስ ፡
አቶ ፡ ተኽለ ፡ ካሕሳይ ፡

አቶ ፡ አርአያ ፡ ገብረሥላሴ ፡

አቶ ፡ አስፍሐ ፡ አብተው ፡

አቶ ፡ አፈወርቅ ፡ ጀርጀ ፡

አቶ ኢሳይያስ ፡ ሀብተ ፡ ሥላሴ ፡

ግራዝማች ፡ እዮብ፡ ተኽሉ ፡

አቶ ፡ ከሊፋ ፡ መሐመድ ፡ ዓሊ ፡

ፍስአቶ ከሰተ፡ ፍስሐየ ፡

አቶ ፡ ኪሕሳይ ፡ አስፍሐ ፡

አቶ ፡ ካሣሁን ፡ ደረሰ ፡

የሻምበል ፡ ከብረ ፡ አብ ፡ በርሄ ፡

አቶ ፡ ክብሮም ፡ ዘይሉ ፡

አቶ ፡ ወልዱ ፡ በርሄ ፡

ያምሳ ፡ አለቃ፡ወረታ፡ ተክለሃይማኖት

አቶ ፡ እቁባዝጊ ፡ ኢድከመ ፡

ያምሳ ፡ አለቃ ፡ ዮሐንስ ፡ተክለየስ ፡

አቶ ፡ ገብረሚካኤል ፡ ብሥራት ፡

አቶ ፡ ገብረሥላሴ ፡ ገረንሰኤ ፡

አቶ ፡ ገብረእግዚአብሔር ፡ ተስፋ ፡ ሚካኤል ፡

አቶ ፡ ገብረትንሣኤ ፡ ወልደሥላሴ ፡

የሻለቃ ፡ ግርማይ ፡ ካሣሁን ፡

አቶ ፡ ጸሐየ ፡ ዮሐንስ ፡

አቶ ፡ ጸጋይ ፡ ባይ፦ ፡

የአሥር ፡ አለቃ ፡ ፋሲል ፡ ደምሳስ ፡